## ትውፊት

### 1/ ስንክሳር፡- መስከረም ሰባት

መስከረም 7 ቀን 2008 ዓ.ም

አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም መስከረም ሰባት በዚች ቀን የከበረና የተመሰገነ የእስክንድርያ አገር ሊቀ ጳጳሳት አባ ዲዮስቆሮስ ዐረፈ። እርሱም ለአባቶች ሊቃነ ጳጳሳት ሃያ አምስተኛው ነው። ስለቀናች ሃይማኖት ታላቅ ተጋድሎን ከተጋደለ በኋላ ዕረፍቱ በተሰደደበት በደሴተ ጋግራ ሆነ።

ይህም እንዲህ ነው ንጉሥ መርቅያኖስ ወደሰበሰበው ጉባኤ በጠሩት ጊዜ ብዛታቸው ስድስት መቶ ሠላሰ ስድስት የሆነ ታላቅ ጉባኤን አየ። እንዲህም አለ ይህ ታላቅ ጉባኤ እስቲሰበሰብ ድረስ በሃይማኖት ላይ የተገኘው ጉድለት ምንድነው።

ይህ ጉባኤ የተሰበሰበው በንጉሥ ትእዛዝ ነው አሉት። እንዲህም አላቸው ይህ ጉባኤ ስለ ክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቢሆን ኖሮ እኔ ተቀምጬ እግዚአብሔር በሰጠኝ በአንደበቴ እናገር ነበር፣ ግን የዚህ ጉባኤ መሰብሰብ በንጉሥ ትእዛዝ ከሆነ የሰበሰበውን ጉባኤ ንጉሡ እንዳሻው ይምራ።

ከዚህም በኋላ አንዱን ክርስቶስን ከተዋሕዶ በኋላ ሁለት ባህርይ ሁለት ምክር የሚያደርግ የክህደት ቃል በውስጡ የተጻፈበትን የሮሜ ሊቀ ጳጳሳት ልዮን የላከውን ደብዳቤ የከበረና የተመሰገነ ዲዮስቆሮስ ቀደደ።

በመንፈስ ቅዱስ የሚናገር የከበረ ዲዮስቆሮስም በጉባኤው ፊት እንዲህ ብሎ አስረዳ፣ ሰው እንደመሆኑ ወደ ሠርግ ቤት የጠሩት ጌታችን ኢሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ ውኃውን ለውጦ ወይን ያደረገው ከሀሊ ስለሆነ ሰውነቱና መለኮቱ በሥራው ሁሉ የማይለይ አንድ ነው።

ደግሞ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አባ ቄርሎስ ከተናገረው የአካላዊ ቃል ተዋሕዶ እንደ ነፍስና ሥጋ፣ እንደ እሳትና ብረት ተዋሕዶ ነው ያለውን ቃል ምሥክር አድርጎ በማምጣትም አስረዳ። እሌህም ሁለቱ የተለያዩ ጠባዮች ስለ ተዋሕዷቸው አንድ ከሆኑ እንዲሁም የክብር ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ አንድ መሲሕ አንድ ጌታ አንድ ባህርይ አንድ ምክር ነው እንጂ ወደ ሁለት አይከፈልም አላቸው።

ከዚያም ከተሰበሰበው ጉባኤ ውስጥ ማንም ሊከራከው የደፈረ የለም ከውስጣቸውም የእግዚአብሔር ጠላት ስለሆነው ስለ ከሃዲው ንስጥሮስ በኤፌሶን ጉባኤ አስቀድሞ ተሰብስበው የነበሩ አሉ።

ወደ ንጉሥ መርቅያኖስና ወደ ሚስቱ ንግሥት በርክልያ ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ከአባ ዲዮስቆሮስ በቀር ስለ ሃይማኖት ትእዛዛችሁን የሚቃወም የለም ብለው ነገር ሠሩበት።

ቅዱስ ዲዮስቆሮስንም ወደ ንጉሥ አቀረቡት ከእርሱም ጋር ታላላቅ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ከጉባኤው የሆኑ ነበሩ። ከጥዋትም እስከ ማታ እርስ በርሳቸው ሲከራከሩ ዋሉ። የከበረ ዲዮስቆሮስም የቀናች ሃይማኖቱን አልለወጠም። ንጉሡና ንግሥቲቱ በእርሱ ተቆጥተው እንዲደበድቡት አዘዙ፣ ስለዚህም ደበደቡት ጽሕሙን ነጩ፣ ጥርሶቹንም ሰበሩ እንዲህም አደረጉበት።

ከዚህም በኋላ የተነጨውን ጽሕሙን ያወለቁትንም ጥርሶቹን ሰብስቦ ወደ እስክንድርያ አገር ላካቸው እነሆ የቀናች ሃይማኖት ፍሬ ይህ ነው አላቸው። ለጉባኤውም የተሰበሰቡ ኤጲስ ቆጳሳት በዲዮስቆሮስ ላይ የደረሰውን መከራ በአዩ ጊዜ እጅግ ፈሩ፣ በእርሱ የደረሰ በእነርሱ ላይ እንዳይደርስ ስለዚህም ከመናፍቁ ንጉሥ ከመርቅያኖስ ጋር ተስማሙ።

በሲኦል ውስጥ ይቆርጡት ዘንድ ባለው ምላሳቸውም ለክርስቶስ ሁለት የተለያዩ ባሕርያት አሉት ብለው በንጉሱ መዝገብ ላይ በእጆቻቸው ጽፈው ፈረሙ። ቅዱስ ዲዮስቆሮስም ያን በውስጡ የጻፉበትን ደብዳቤ ያመጡለት ዘንድ ወደእሳቸው ላከ፣ እነርሱም ላኩለት፣ እነርሱ እንደጻፉ በውስጡ እርሱ የሚጽፍ መስሏቸዋልና።

እርሱ ግን አባቶቻችን ሐዋርያት ከአስተማርዋት ከቀናች ሃይማኖት በኒቅያ የተሰበሰቡ ሃይማኖታቸው የቀና ሦስት መቶ አሥራ ስምንት ኤጲስ ቆጶሳት አባቶቻችን ከሠሩት ሕግ የሚወጣውን ሁሉ በደብዳቤው ግርጌ ጽፎ አወገዘ።

መናፍቁ ንጉሥም ተቆጥቶ ጋግራ ወደምትባል ደሴት እንዲአግዙት አዘዘ ወደዚያም ወሰዱት። ከእርሱ ጋር የአገረ ቃው ኤጲስ ቆጶስ አባ መቃርስ አብሮ ተሰደደ። ሌሎችም ዐራት መነኮሳት የሸሹ አሉ።

እሊህም ስድስት መቶ ሠላሳ ስድስት ኤጲስ ቆጶሳት ተቀምጠው በኬልቄዶን ለራሳቸው መመሪያ የሚሆናቸውን ሥርዓት ሠሩ።

የከበረ ዲዮስቆሮስም በአጋዙት ጊዜ ከዚያች አገር ኤጲስ ቆጶስ ጭንቅ የሆነ መከራ ደረሰበት። ኤጲስ ቆጶሱ ንስጥሮሳዊ ስለሆነ ታላቅ ጉስቁልናንም አጎሳቆለው፣ በእጆቹ ላይ ድንቆች ታላላቅ ተአምራቶችን እግዚአብሔር

እስከገለጠ ድረስ።

የደሴቲቱም ሰዎች ሁሉ ሰገዱለት አከበሩት፣ ከፍ ከፍም አደረጉት፣ እግዚአብሔርም የመረጣቸውን በቦታው ሁሉ ያከብራቸዋልና።

አባ ዲዮስቆሮስም አባ መቃርስን አንተ በእስክንድርያ አገር የሰማዕትነትን አክሊል ትቀበል ዘንድ አለህ አለው። ከዚያም በኋላ ከምእመናን ነጋዴዎች ጋር ወደ እስክንድርያ ላከው፣ በእርሱ ላይ ትንቢት እንደተናገረ ገድሉን በዚያ ፈጸመ።

የከበረ አባት ዲዮስቆሮስ ግን መልካም ተጋድሎውን በፈጸመ ጊዜ ክብር ግባውና እግዚአብሔርንም አገልግሎ ከዚህች ኃላፊት ከሆነች ኑሮው ወጥቶ ሔደ፣ የሃይማኖቱንም ዋጋ አክሊልን ተቀብሎ ወደ ዘላለም ዕረፍት ገባ፣ ያረፈውም በዚያች በደሴተ ጋግራ ነው፣ ሥጋውንም በዚያ አኖሩ።

ለእግዚአብሔርም ምስጋና ይሁን እኛንም በዚህ አባት ጸሎት ይማረን፣ በረከቱም ከእኛ ጋር ጋራ ትኑር ለዘላለሙ አሜን።

ምንጭ፡- መጽሐፈ ስንክሳር ከማስከረም እስከ የካቲት፣አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ኣሳታሚ ድርጅት፤1994 ዓ.ም፣ ገጽ 23-25።

< ወደኋላ ወደፊት >

Miko ZE Ethiopia

በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ትምህርት በኹለት ትምህርቶች የሚጠቃለል

ነው።

2/ ዶግማ እና ቀኖና ተብሎ።

1. ዶግማ

ዶከይን ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲኾን በጥሬው አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ አዋጅ ማለት ቢኾንም በምሥጢራዊ ማለትም በቤተ ክርስቲያናዊ ትርጓሜው ግን ሃይማኖት (የእምነት መሠረት) ማለት ነው። በመኾኑም ዶግማ የተደነገገ ሳይኾን የተገለጠ ነው። መገኛውም እግዚአብሔር ነው። ከሰው ሊፈጠር አይችልም። ከእግዚአብሔር የተሰጠ እውነት ነው። በማኛኛውም አካል (በሲኖዶስም ጭምር)፣ በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛውም ኹኔታ (በሞትም በሕይወትም) የማይለወጥ ማንነት አለው።

ዶግማ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርተ ሃይማኖት ነው ብለናል። ስለ ቅድስት ሥላሴ፣ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ (ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መኾኑን፣ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና እንደተወለደ፣ እንደ ተሰቀለ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ፣ ዳግመኛ በክበበ ትስብእት እንደሚመጣ)፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ስለ ምሥጢረ ቁርባን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ክብረ ድንግል ማርያምና ክብረ ቅዱሳን የምንማው እንጂ ማናችንም ልናሻሽለው አንችልም። እንኳንስ አንድ ግለሰብ ይቅርና ሲኖዶስም ቢኾን አለመለወጡን፣ አለመፋለሱን ይመረምራል እንጂ መጨመር ወይም መቀነስ አይችልም። ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- “ነገር ግን (ሐሳባችንን ቀይረን) እኛ ብንኾን ወይም ከሰማይ መልአክ

ከሰበክንላችት ወንጌል የሚለይ ወንጌልን የሚሰብክላችት የተረገመ ይኹን"
ያለውም ስለዚኹ ነው /ገላ.1፥8/።

2. ቀኖና

ቀኖና ማለት ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ፍርድ፣ ቅጣት፣ መጠን፣ ልክ ማለት ነው /ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ገጽ 799/። በግሪኩ ካኖን ሲኾን በዕብራይስጡ ቃኒህ ይሉታል። ይኸውም አንድን ነገር ለመለካት፣ ለመመዘን፣ ትክክል መኾኑንና አለመኾኑን ለመለየት፣ መጠኑን ለማወቅ የሚያገለግል መለኪያ ወይም መስፈርት ነው።

ማኅበረ ሰብእ እስካለ ድረስ ሕግ አለ። ሕግ እንዲኖር የኹለት ሰዎች በአንድ ላይ መኖር በቂ ነውና። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ "አሐቲ ጉባኤ" እንዲል የምእመናን ስብስብ ስለኾነች የራሷ ሕግ አላት። አባቶች "ያልተገራ ፈረስ የባለቤቱን ጥርስ ይሰብራል" እንደሚሉት ይኽ የምእመናን ስብስብ ሰላማዊ እንዲኾን የሚያደርገው የቤተ ክርስቲያን ሕግ ወይም ሥርዓትም ቀኖና ይባላል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው ሕግ ኹለት ዓይነት ነው፤ ተፈጥሮአዊ ሕግና የስምምነት ሕግ። የተፈጥሮ ሕግ የምንለው የእግዚአብሔርን ሕግ ነው። ሰዎች ይኽን የእግዚአብሔር ሕግ ሊለውጡት አይችሉም። ለምሳሌ ወንድ ከሴት ጋር መጋባት አምላካዊ ሕግ ነው። ግብረ ሰዶማዊነትም ይኽን የተፈጥሮ ሕግ የሚቃረን ነው። ፈረስና አህያ ተዳቅለው በቅሎን ይወልዳሉ። ነገር ግን በቅሎ ራሷን መተካት አለመቻሏ ከሕገ ተፈጥሮ ውጪ የተወለደች መኾኗን ነው የሚነግረን። ጠጣና ዝንጀሮ ተዳቅለው የሚወልዷቸው

እንስሳትም አሉ። ነገር ግን ልክ እንደ በቅሎ ራሳቸውን መተካት አይችሉም። ለምን? ስንልም ከሕገ ተፈጥሮ ማለትም ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ የተወለዱ ናቸውና። ስለዚኽ ተፈጥሮአዊ ሕግጋትን ተቃርነን የምናደርጋቸው ነገሮች ትርፋ ድካምና በራስ ላይ ጉዳትን መጨመር ብቻ ነው የሚኾነው።

የስምምነት ሕግ የምንለው ደግሞ በፓርላማ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በቤተ ክርስቲያን ደግሞ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣውን ሕግ ማለታችን ነው። ምንም እንኳን የስምምነት ሕግ ብለን ብንጠራውም ቅዱስ ሲኖዶስን የሚመራው መንፈስ ቅዱስ ስለኾነ እንዲኹ የሰዎች ስምምነት ነው ብለን የምንወስደው ወይም ዝቅ አድርገን የምንመለከተው አይደለም። እነዚኽ ሕጎች ኹለት መሠረታዊ ጠባያት አሏቸው። ጥቅል ወይም ዝርዝር ሕጎች ሊኾኑ ይችላሉ።

የስምምነቱ ሕግ ጊዜያዊም ለረዥም ጊዜ የሚቈይም ሊኾን ይችላል። ለምሳሌ እግዚአብሔር በምሕረት ዓይን እንዲያየንና በቤተ ክርስቲያን እንዲኹም በዓለም ላይ የተጋረጡትን ችግሮች እንዲያርቅ ቅዱስ ሲኖዶስ ለኹለት ሳምንት ጾምና ጸሎት ቢያውጅ ጊዜአዊ ሕግ (ቀኖና) ይባላል። በዓመት ሰባት የአዋጅ አጽዋማት መኖራቸው ግን በሕይወት እስካለን ድረስ የሚገዛን ቀኖና ነው።

የስምምነት ሕግ የተጻፈም ያልተጻፈም ሊኾን ይችላል። ያልተጻፈ መኾኑ ግን ሕግ ከመኾን አይከለክለውም። ካልተጻፈ ተብሎ አይጣስም። እያንዳንዳችን የአንዳችንን ፍላጐት ለመጠበቅ ተፈጥረናልና /ዘፍ.4/።

## ቀኖና ቤተ ክርስቲያን

ቀኖና የሚለው ቃል እንደ አኹኑ ለቤተ ክርስቲያን ከማገልገሉ በፊት ሕዝቡ

በማንኛውም የዕለት ተዕለት ሕይወቱ የሚዳኝበት ሕግን ያካተተ ነበር። ቤተ ክርስቲያናዊ (ክርስቶሳዊ ሕግ) እና ሕዝባዊ (ቄሳራዊ) ሕግ ተብሎ የተለየው በኋላ ነው /The Oxford Dictionary of the Christian Church, pp 277/። ቤተ ክርስቲያንም መዠመሪያ አከባቢ ላይ ቀኖና የሚለውን ቃል ስትጠቀም የመጻሕፍቶቿን ዝርዝር፣ የሥርዓተ አምልኮቷን አፈጻጸም፣ የምሥጢራት ቤተ ክርስቲያንን አፈጻጸም፣ የአንድ ክርስቲያን ሥነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት ለመግለጥ ነበር። ይኽ ቀኖና እንዲኖራት ምክንያት የኾናትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይከሰቱ የነበሩት አለመግባባቶች ናቸው። በተለይ አንዳንድ ከእምነትም ከምግባርም የሚወጡ ሰዎች ሲገኙ ምእመናን ግራ እንዳይጋቡ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ይወጣ ነበር። እንደ ችግሩ መጠንም የሚወጣው ሕግ (ቀኖናው) ዳርቻው አጥቢያዊ፣ ወይም ሀገረ ስብከታዊ፣ ወይም ሀገራዊ፣ ወይም ዓለማቀፋዊ ይዘት ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ ትንሽ ቆየት ብለን እንደምንመለከተው በጉባኤ ኒቅያ የተደነገጉት ቀኖናት ዓለማቀፋዊ ይዘት ያላቸው ቀኖናት ናቸው /Ibid/።

ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊት ካልኾነች እውነተኛ አይደለችም። የእግዚአብሔርን ልጅ ማወቅ ብቻውን ትርጉም የለውም፤ አጋንንትም ያውቁታልና። ትርጉም የሚኖረው ስናምንና ስንጠመቅ ነው። ይቅርታ ሰላምን እንደሚሰጥ ይታወቃል፤ ይቅር ካላልን ግን ትርጉም የለውም። በሌላ አገላለጽ እምነታችንን የምናከናውንበት ዝርዝር ቀኖና ከሌለ እምነታችን ትርጉም አልባ ነው፤ ምክንያቱም ቀኖና “እምነታችንን እንዴት እንፈጽም?” ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ዝርዝር አፈጻጸም ነውና።

የቤተ ክርስቲያን ቀኖናት የተሰጡት በሐዋርያት ነው። ለሕዝቡ ያስተማሩትም እነርሱ ናቸው። በእነርሱ ወንበር የተቀመጡት ሊቃነ ጳጳሳትም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት ጊዜውን የዋጀ ቀኖና ይሠራሉ።

ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከሌላ የሚሠለጥነው ዲያብሎሳዊ ሕግ ነው። የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማም ሰዎችን ሥርዓት አስይዞ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖራቸው ማድርግ ነው። እንደ ምሳሌ ብንጠቅስ አርዮስን ለመገሰፅ ቤተ ክርስቲያን 25 ዓመት ፈጅቶባታል። የኢትዮጵያ እስር ቤቶች እንኳን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ደብረ ሐይቅ (የግራኝ መሐመድ ወንድም የታሰረበት)፣ ደብረ ዳሞ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ፣ ክብራን ገብርኤል፣ ግሸን ደብረ ከርቤ እና ሌሎች ታላላቅ ገዳማት ነበሩ። ይኽ የኾነበት ዋና ምክንያትም የቀኖና ዓላማ ሰዎች እንዲታረሙ ማድረግ እንጂ ሰውን መቅጣት ስላልኾነ ነው። አጼ ቴዎድሮስ አንድን ሌባ ያገኛሉ። ይዘዉም እጁን ይቈርጡታል። በዚያን ጊዜ የነበሩ ታላቁ ሊቅ አለቃ አካለ ወልድም በቅኔ አድርገው አጼ ቴዎድሮስን ወረፏቸው። አለቃ አካለ ወልድ ይኽን ያደረጉበት ዋና ምክንያትም "ሰውዬው እጁ ስለተቈረጠ ከዚያ በኋላ መሥራት አይችልም፤ የሰው ጥገኛ ነው የሚኾነው። ቀኖና ሊሰጠው ይገባ ነበር" ሲሉ ነው፤ እንደተናገርን የቀኖና ዓላማ ሰውን ማዳን እንጂ ሰውን መጉዳት ወይም ጫና መፍጠር አይደለምና።

"ሕግ ከጽዮን ይወጣል" /ኢሳ.2፥3/ እንደተባለ የሕግ ምንጭ ቤተ ክርስቲያን ነች። ሕግ አውጪ ብቻ ሳትኾን ሕግ ተርጓሚዋና ሕግ አስፈጻሚዋም ርሷ ራሷ ናት። ሕጓም ዓለምአቀፋዊ ዳርቻ አለው። ቤተ ክርስቲያን ባለችበት ኹሉ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንም አለ። አትስረቅ፣

አትግደል፣... የሚሉት የቤተ ክርስቲያን ሕጎች ናቸው። በመኾኑም እነዚኽ ሕጎች በማንኛውም ቈሣራዊ ሥርዓት፣ በማንኛውም ዓይነት ቋንቋ፣ በማንኛውም ዓይነት ማኅበረ ሰብእ ውስጥ አሉ። የሥላሴ አጥር ዳር ድንበር የለውምና የቤተ ክርስቲያን ሕግም ዳር ድንበር የለውም። ጾም የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው። አፈጻጸሙ ግን እንደየቦታውና እንደየሰዉ ኹናቴ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ በዓፋር የሚኖር ክርስቲያን እስከ ዘጠኝ ሰዓት ካልጾምክ ካልነው በውኃ ጥም እንገድሏለን። አዲስ አበባ ላይ የሚኖረው ክርስቲያን ዓፋር ላይ እንደሚኖረው ክርስቲያን 4፡00 ሰዓት ላይ ውኃ ልጠጣ ቢል ግን የተለየ ምክንያት ከሌለው በቀር ተቀባይነት የለውም። እንዲኽ ሲባል ግን እያንዳንዱ ሰው በራሱ ሕሊና ያለበትን ኹናቴ እያመዛዘነ በራሱ ውሳኔ የሚያደርገው ነው ማለታችን አይደለም። እንዲኽ ዓይነት ለየት ያለ ቀኖና (Exceptional Canon) የሚያወጣው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጋዊ አካል ብቻ ነውና "ይኼ እኮ ቀኖና ነው፤ ባናደርገውም ምንም ችግር የለውም" ከሚለው ግላዊ አስተሳሰብ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የራሱ የኾነ ልዩ ባሕርያት አሉት።

· ሥልጣን ባለው አካል የሚደነገግ፣ የሚተገበር፣ የሚሻሻል ነው። ሲደነገግም ሲሻሻልም በግለሰቦች የግል ፍላጐት ወይም ፈቃድ የሚደነገግ ወይም የሚሻሻል አይደለም።

· ሃይማኖታዊ ይዘት አለው። ምክንያቱም ዓላማው ሰውን ኹሉ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ማፍለስ ስለኾነ ቈሣራዊ ይዘት የለውም። ቢኖርም እንኳን አንድ ክርስቲያን በዚኽ ምድር የሚኖረው ቆይታ ከሰማያዊ ሕይወቱ ጋር ሳይጣረስበት እንዴት መኖር እንዳለበት የሚያስረዳ ነው።

· የሰው ልጅ ከሚችለው በላይ ሸክምን አይጭንም፤ “ሸክሜ ቀሊል ነው” እንዲል /ማቴ.11፥29/።

· የሸላሚነትና የቀጪነት ሥልጣን አለው። ቁሣራዊ ሕግ የሽላሚነት ይዘት የለውም። በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ግን ለምሳሌ ተጋድሎአቸውን በድል ያጠናቀቁት ክርስቲያኖች ቀን ተለይቶላቸው፣ ታቦት ተቀርጾላቸው በምእመናን ዘንድ ክብርን እስከ ማግኘት ይደርሳሉ። በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ የዘለዓለም አክሊል ዘውድ አለው።

· የአምልኮ ይዘት አለው። በውስጡ ጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት እና የመሳሰሉትን ኹሉ ያካትታል።

· የመመዘን ጠባይ አለው። ለምሳሌ የቃየን መሥዋዕት ያልስመረችው መሥዋዕት ስላላቀረበ ሳይኾን በሕጉ መሠረት አሰስ ገሰስ ኾኖ ስለተገኘ ነው /ዘፍ.4/።

· በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ የተደነገገ አይደለም።

· ሰዎችን ደስ ለማሰኘት አይወጣም፤ የሚወጣው እግዚአብሔር ደስ ለማሰኘት ብቻ ነው። “ለዓለም ከሚመች ከንቱ ልፍለፋ ራቅ” እንዲል ለዓለም የሚመች ቀኖና አይወጣም። ቀኖና የሚወጣው የምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያድግና ምእመናን በሚኖሩበት ማኅበረ ሰብእ ውስጥ አርአያ እንዲኾኑ ነው።

· አንጻራዊ ጽድቅ ስለሌለ አንጻራዊ ቀኖናም የለም። ጥቁሩን ጥቁር ነጩን ነጭ የሚል እንጂ የተድበሰበሰ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አታወጣም፤ እንዲኽ ካልኾነ የውጫሌ ሕግ ነው። በዓለማዊ ሕግ የወንጀሉ መጠን ይታያል። በቤተ ክርስቲያን ሕግ ግን ወንጀል ወንጀል ነው።

የቀኖና ምንጮች

ዛሬ ላለው የቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና ምንጮቹ ልዩ ልዩ ቢኾኑም ጠቅለል ባለ መልኩ ግን እንደሚከተለው ከፍለን ማየት እንችላለን።

ሀ) የሐዋርያት ሲኖዶስ

እነዚኽ መጻሕፍት በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. 81 ተብለው ከሚታወቁት መጻሕፍት የሚካተቱ ሲኾኑ ሐዋርያት በየጊዜው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እየተሰበሰቡ የደነገጓቸው እጅግ ጠቃሚ የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው። እነርሱም መጽሐፈ ዲድስቅልያና መጻሕፍተ ሲኖዶሳት (ትእዛዝ፣ ግፅው፣ አብጥሊስ፣ ሥርዓተ ጽዮን) ናቸው። ሲኖዶስ የተባለውና አራት ክፍል ያለው መጽሐፍ በውስጡ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ስለ አገልጋዮች ማዕረጋት ቀኖና ይናገራል። መጽሐፈ ዲድስቅልያ ደግሞ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እና ሥርዓተ አምልኮን በዝርዝር ይናገራል።

እናስተውል! የጌታ ትእዛዛት በሙሉ ዶግማ ነው። ጾም፣ ጸሎት፣ ጥምቀት፣ ቁርባን፣ ንስሐ፣ ከወንድም ጋር መታረቅ...ወዘተ ዶግማ ነው። ቀኖና የሚኾነው ዝርዝር አፈጻጸሙ ላይ ሲኾን ነው። ቀኖና ከሐዋርያት የሚዠምረውም ለዚኹ ነው። በመኾኑም አንድ ሰው ተነሥቶ ጾም አያስፈልግም ቢል የቀኖና ሳይኾን የዶግማ ጥሰት ነው።

ለ) ዓለም አቀፍ ጉባኤያት

ጉባኤያት ዓለማቀፋውያን ጉባኤያት የሚባሉት ከኹሉም አብያተ ክርስቲያናት የመጡ ተወካዮች ሲኖሩበት ነው። የጉባኤው መነጋገሪያ አጀንዳም ዓለማቀፋዊ መኾን አለበት። የተወሰነው (የሚወሰነው) ውሳኔም በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተፈጻሚ መኾን አለበት። የነገሩ ጉዳይ

ለአንዲት ሀገር ብቻ የሚተው መኾን የለበትም። ለምሳሌ በ325 ዓ.ም. የተካሔደው የኒቅያ ጉባኤ ዓለማቀፋዊ አጀንዳን የያዘ (ዓለም ስለመዳኑና ስላለመዳኑ)፣ ከኹሉም አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች የነበሩበት፣ ውሳኔውም በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተፈጻሚነት የነበረው ነው። በኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ሦስት ሲኾኑ፤ ምሥራቃውያን 7፥ ካቶሊኮች ደግሞ 20 ይቀበላሉ።

ኦሬንታል አርቶዶክሶች የምንቀበላቸው ሦስቱም ጉባኤያት ጉባኤ ኒቅያ (በ325 ዓ.ም. የተካሔደ)፣ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ (በ381 ዓ.ም. የተካሔደ) እና ጉባኤ ኤፌሶን (በ431 ዓ.ም. የተካሔደ) ናቸው። በእነዚኽ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ብዙ ቀኖናዎች ተደንግገዋል። ለምሳሌ በጉባኤ ኒቅያ ከተወሰኑት ቀኖናት የትንሣኤ በዓል እሑድ መከበር እንዳለበት፣ ስለ አርዮስ ጉዳይ፣ ስለ መጻሕፍት ጉዳይ፣ ስለ አራቱ መንበረ ፓትሪያሪኮች ይገኙባቸዋል።

ሐ) ብሔራውያን ጉባኤያት

ከዓለማቀፋውያን ጉባኤያት በተጨማሪ በየአካባቢው ጉባኤያት ሊደረጉ ይችላሉ። ለምሳሌ በቅዱስ ያሬድ ዜማ ላይ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይዋ አይደለም። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ አይደለም ብለን ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስር ኾነን ያሬዳዊ መዝሙር አያስፈልገንም ወይም በኦርጋንና በፒያኖ እንዘምር ማለት አንችልም። እነርሱ በያሬዳዊ መዝሙር ስላልዘመሩ ብለንም ሃይማኖታዊ (የዶግማ) ወይም የቀኖና ችግር አለባቸው አንልም፤ ውሳኔው በብሔራዊ ጉባኤ

የተወሰነ ነውና።

ከብሔራውያን ጉባኤያት በተጨማሪ ሀገረ ስብከታዊ ጉባኤም ሊደረግ ይችላል። አጥቢያዊ ጉባኤም ሊኖር ይችላል። ነገር ግን በአንድ ሀገረ ስብከት የተወሰነው ውሳኔ በሌላ ሀገረ ስብከት ተፈጻሚ ላይኾን ይችላል። በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራ ቀኖናም በሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይሠራ ይችላል። በኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንድ ገዳማት ላይ ሴቶች አይገቡም የሚባለው የዚያ ገዳም ብቻ ቀኖና ስለሚኾን ነው።

መ) የቅዱሳን አበው ቀኖናት

እነዚኽ ቀኖናት ምንም እንኳን በግለሰብ ደረጃ የተወሰኑ ቢኾኑም ቤተ ክርስቲያን የእኔ ብላ የተቀበለቻቸው ቀኖናት ናቸው። ለምሳሌ ሥርዓተ ምንኩስና የነ አባ እንጦንስ ወይም የእነ አባ ጳኩሚስ ሃይማኖት አይደለም፤ የእነዚኽ ቅዱሳን አባቶች የትሩፋት ሥራ እንጂ። አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስለ ቅዱስ ቁርባን የተናገረው ሥርዓት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. ሥርዓት ኾኖ የቀረውም ከዚኽ አንጻር ነው። የቅዱሳን ገድላትና ድርሳናትም እንደምንጭነት ይጠቀሳሉ።

የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ይዘት

ቤተ ክርስቲያናዊ ቀኖና በውስጡ በጣም ብዙ ነገሮችን ያካተተ ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና፣ የሥርዓተ አምልኮ ቀኖና፣ የአጽዋማት ቀኖና፣ የበዓላት ቀኖና፣ የቅዱሳን ቀኖና፣ የቅዱሳት ሥዕላት ቀኖና፣ የአለባበስ ቀኖና ተጠቃሾች ናቸው። እስኪ ጥቂቶቹን ብቻ እንደማሳያ በአጭር በአጭሩ ለማየት እንሞክር፦

1. የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና

የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና ስንል የመጻሕፍቱ እውነተኛነትን፣ ቅዱስነትንና አምላካዊነትን የተመለከተ ማለታችን ነው፡፡ እነዚኽን ቅዱሳት መጻሕፍት ሰፍረውና ቈጥረው የሰጡንም ሉተራውያን ወይም ካቶሊካውያን ሳይኾኑ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ናቸው፡፡ በተለይም እነ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ በዚኽ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እነዚኽ ቅዱሳን አባቶች የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ለመቀበል ያስቀመጧቸው መስፈርቶች ነበሩ፡፡ ከእነዚኽም መካከል፡-

Ü ወደ ግሪክኛ የተተረጐመ፡፡ አባቶች ይኽን ያሉበት ዋናው ምክንያት አይሁዳውያኑ የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት ካለመቀበላቸው የተነሣ ብሉይ ኪዳንን ቈነጻጽለዉት ስለነበር ነው፡፡ ስለዚኽ ከዚኽ ከተቈነጻጸለው መጽሐፍ ሊመጣ ከሚችለው ግድፈት ለመዳን አይሁዳውያኑ ይኽን እንደሚያደርጉ አስቀድሞ የሚያውቅ እግዚአብሔር በ285 ቅ.ል.ክ. ላይ ወደ ግሪክኛ የተተረጐመው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ መቀበል ግድ ኾኖባቸዋል፡፡

Ü የዕብራውያን ባሕል ያለበት፡፡ አባቶች መጽሐፉ የዕብራውያን ባሕል ያለበት መኾን አለበት ያሉበት ምክንያት እግዚአብሔር አስቀድሞ ለዕብራውያኑ በባሕላቸው ስለነገራቸው ነው፡፡ መጽሐፉ ዕብራዊ ባሕል ከሌለበት ተቀባይነት አያገኝም፡፡

Ü የአብርሃም እምነት ያለበት፡፡ የአብርሃም እምነት መኾን አለበት ሲሉም ከአንድ አምላክ በቀር ወደ ባዕድ አምልኮ የሚመሩትን መጻሕፍት ለመለየት ነው፡፡

የሰባ ሊቃናት ትርጉም የምንለውም ይኽን ቀኖና ተከትሎ የተሠራ ትርጉም ነው፡፡ በ2000 ዓ.ም. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. ያሳተመችው መጽሐፍ ቅዱስ

ትርጒሙ አብዛኛው ከዚኹ ትርጒም የተወሰደ ነው።

እናስተውል! በአንዳንድ የአማርኛ ትርጒሞች ላይ (ለምሳሌ በ1980 ዓ.ም. እትም ላይ) በስሕተት ተጽፎ የምናገኘው ቢኾንም በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ዲዩትሮካኖኒካል የሚባሉ መጻሕፍት የሉም። ዲዩትሮካኖኒካል የሚሉት ካቶሊኮች ናቸው። ይኸውም ተጨማሪ መጻሕፍት ለማለት ነው። ነገር ግን እነዚኽ መጻሕፍት ከመዠመሪያውኑ የነበሩ እንጂ በኋላ የተጨመሩ አይደሉም። ለዚኽ ማረጋገጫውም በ1948 ዓ.ም. ላይ በሙት ባሕር ላይ በተገኙት ጥቅሎች እነዚኽ ተጨማሪ ናቸው ተብለው የታሰቡት መጻሕፍት በዕብራይስጥ ተጽፈው መገኘታቸው ነው። ስለዚኽ አይሁዳውያኑ በ280 ዓ.ም. ላይ ታናክ የሚሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቀኖና ሲሠሩ የሰባ ሊቃናቱን ትርጒም የክርስቲያኖች መጽሐፍ ነው ብለው ስለቈነጻጸሉትና ስለቀነሷቸው እንደተጨማሪ መጻሕፍት ማየት (ዲዩትሮካኖኒካል ናቸው ማለት) በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ያልነበረ ነው።

አኹንም እናስተውል! እነዚኽን መጻሕፍት እንደ ፕሮቴስታንቱ ዓለምም አፖክሪፋ አንላቸውም። አፖክሪፋ ማለት በግሪክኛ የተሰወረ፣ ያልተገለጠ፣ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ ለማለት ነው። ፕሮቴስታንቱ ዓለም ይኽን እንዲል ያደረገው ዋናው ምክንያት ከላይ እንደገለጽነው አንደኛ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍቱን ተጨማሪ ናቸው ስላለችና እነርሱም ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሲወጡ ተጨማሪ የሚለውን ቃል ብቻ ይዘው ተጨማሪ አያስፈልገንም በማለት፤ ኹለተኛ አይሁዳውያኑ የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት ላለመቀበልና ለክርስቲያኖች በነበራቸው የመረረ ጥላቻ በተንኰል

የቈነጻጸሉትን መጽሐፍ ያለምንም ጥያቄ ስለተቀበሉት ነው። ስለዚኽ ራሳችንንና ወንድማችንን ከእንደዚኽ ዓይነት ኦርቶዶክሳዊ ያልኾነ ትምህርት ልንጠነቀቅ ይገባል። አብዛኞቹ የእንግሊዘኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች የተተረጐሙት ከዚኹ አይሁድ ከቈነጻጸሉት ቀኖና የተወሰደ መኾኑንም ማስታወሱ ተገቢ ነው። ደኅና ነው ተብሎ የሚታሰበው "Revised Standard Version" የሚባለው ነው።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የሐዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ለመለየት የተጠቀሙበት መስፈርትም አለ። እርሱም፡-

Ü ሐዋርያት ወይም የሐዋርያት ደቀ መዛሙርት የጻፉት መኾን አለበት፤

Ü ከ99 ዓ.ም. በፊት መጻፍ አለበት። ይኽን ያሉበት ዋና ምክንያትም ከ105 ዓ.ም. በኋላ የግኖስቲኮች የክሕደት መጻሕፍት በስርጭት ላይ ስለነበሩ ነው።

Ü የክርስቶስና የሐዋርያት ትምህርት የሚገልጽ መኾን አለበት።

አንድ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ቅዱሳት መጻሕፍትን (አሥራውም ይኹኑ አዋልድ) ሲለይ ከምንም በላይ ማየት ያለበት ቊጥሩን (81፣ 66፣ 73፣ 76 የሚለውን) ሳይኾን ኦርቶዶክሳዊ ይዘታቸውን ነው። አንድ መጽሐፍ ኦርቶዶክሳዊ ይዘት እንዳለው የሚታወቀውም፡-

· ነገረ እግዚአብሔርን የሚያስክድ ካልኾነ። ለምሳሌ የጀሆቫ ዊትነስ፣ የሞርሞን አማኞች ያዘጋጁት "መጽሐፍ ቅዱስ" ፍጹም ክሕደት ነው።

· የሚርት ይዘት ከሌለው። ምንም እንኳን ተጨማሪ ሥራ የሚጠይቅ ቢኾንም የዚኽ ጽሑፍ አዘጋጅ እስከ አኹን ድረስ ባለው መረጃ መሠረት በሐዲስ ኪዳን ኅቡእ ስም የለም። ምንም እንኳን በአንዳንድ የቤተ

ክርስቲያናችን ድርሳናት ላይ እንዲኽ ዓይነት ጽሑፍ ብናገኝም ወደ ኋላ ስንሔድና የዚያ ድርሳን ጥንታዊውን የብራና ጽሑፍ ስንመለከት ግን ጸ፣ጸ፣ጸ፣ጸ፣ጸ፣ጸ፣ ጨ፣ ጨ፣ ጨ፣ ጨ፣ ገ፣ ገ፣ ገ፣ ገ፣ ገ… የሚል ኅቡእ ስም የለውም። እነዚኽ ኅቡእ ስሞች በኋላ ላይ በስርዋፅ የገቡ ናቸው። አኹን አኹን የሚታተመውን ድርሳነ ሚካኤልን እንደ አንድ ማሳያ ብንወስደው ከ15ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በነበረው የድርሳነ ሚካኤል የብራና ጽሑፍ ላይ እንዲኽ ዓይነት ኅቡእ ስም የለውም። ዘወትር ለጸሎት በምንጠቀምበት በወንጌል፣ በመዝሙረ ዳዊት፣ ወይም በውዳሴ ማርያም ኅቡእ ስም የለም። ኅቡእ ስም ተብሎ በብዛት የምናገኘው በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ በግለሰቦች በሚታተሙት መጻሕፍት ላይ ነው /የቃል መረጃ ከመምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል፣ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቀኖና ቤተ ክርስቲያን መምህር/። በመኾኑም በቤተ ክርስቲያናችን በአዋልድ መጻሕፍት ቀኖና ዙርያ ብዙ የሚቀር ሥራ እንዳለ ያመለክታል። የሚመለከታቸው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም የድርሻቸውን እንደሚወጡ እምነታችን ነው።

· እምነታችንን ከእግዚአብሔር አውጥቶ ለሌላ አካል አሳልፎ የሚሰጠን ካልኾነ። ለምሳሌ ይኽን ቃል ደጋግመኽ በለው ካለ፤ የፈጣሪን ሥራ በሌላ የሚቀይር ከኾነ፤ ከዚኽ ከዚኽ የሚያድኑ ጸሎቶች የሚል ከኾነ፤ በትራስኽ ላይ ብትንተራሰው ካለ፤ ይኽን ክታብ በአንገትኽ ላይ ብታንጠለጥለው የሚል ዓይነት ከኾነ ያለ ምንም ቅድመ ኹኔታ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት እንዳልኾኑ ዐውቀን ልንጥላቸው ይገባል።

2. የቅዱሳን ቀኖና

በቀኖና ወይም በሥርዓት ደረጃ ቅዱሳንን ማክበር የተዠመረው ከኹለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንሥቶ ነው። ነገር ግን ይኽን ያደረገው ቅዱስ ሲኖዶስ ሳይኾን ሕዝቡ ወይም ምእመኑ ራሱ ነው። በዚኽም ቀድመው ይታሰቡና ይከበሩ የነበሩት ቅዱሳን ሰማዕታት ናቸው። ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዠምሮ ግን አንዳንድ ሰዎች በራሳቸው እይታ ቅዱስ እንደኾነ የሚያስቡትን ኹሉ ቅዱስ ለማስባል ስለተነሣሡ ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ ደረጃ ቀኖና ቅዱሳን ማውጣት ዠመረች። ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቅዱሳን ማውጣት ዠመረች ማለት ግን ለሰዎቹ ቅድስናን ሰጠች ማለት ሳይኾን ለቅድስናቸው ዕውቅናን ሰጠች ለማለት ነው። ይኸውም ከትሩፋታቸው ብዙ እንድንማር፣ በቃል ኪዳናቸው እንድንጠቀም፣ አሰረ ፍኖታቸውን እንድንከተል፣ አማላጅነታቸውን እንድንጠይቅ ነው።

አንድን ቅዱስ ቅዱስ ለማለት መስፈርቶች አሉት። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያኽል፡-

· ከምንም በፊት ክርስቲያን መኾን አለበት። አምኖ የተጠመቀ፣ ቅዱሳት ምሥጢራትን ሲፈጽም የኖረና ከእኩያት ጋር የተጋደለ መኾን አለበት። አለበለዚያ ክርስቲያን ሳይኾኑ (ካቶሊክም ፕሮቴስታንትም ጭምር) የፈለገ ያኽል በጎ ምግባር ቢኖራቸውም ቅዱሳን አይባሉም።

· በክርስቲያናዊ ምግባራቸው የታወቁ። ሃይማኖት ያለ ምግባር የሞተ ነውና። እንዲኽ ሲባልም ፈጽመው ኃጢአት ያልሠሩ ለማለት አይደለም፤ እንዲኽ ያለ ዕሩቅ ብእሲ ከእመቤታችን በቀር ማንም አይገኝምና።

· ገቢረ ተአምራትን የፈጸሙ። እንዲኽ ሲባልም ተአምራትን ማድረግ ብቻውን መስፈርት ሊኾን እንደማይገባ ሊታወቅ ይገባል /ማቴ.7፡21/።

· ቅዱሳኑ ካረፉ በኋላ ዓጽማቸው ሕሙማንን ከፈወሰ፤ ባረፉበት ቦታ ጠበል ከፈለቀ።

· ለየት ያለ አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ካበረከቱ። ለምሳሌ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. እነ ቅዱስ ላሊበላ፣ እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ እነ አቡነ ጴጥሮስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረጉትን አስተዋጽኦ ማስታወሱ በቂ ሊኾን ይችላል።

እንዲኽ በቀኖናው መሠረት ቅዱስ የተባለው ታላቅ ሰው ቅድስና ሲሰጠው የሚከተሉት ነገሮች ይፈጸሙለታል፡-

v በስሙ ቤተ ክርስቲያን ይታነጽለታል፤

v ገድል ይጻፍለታል፤

v በዓል ይደረግለታል፤

v ቅድስናውን አጕልቶ የሚያሳይ ሥዕል ይሣልለታል፤

v ዐፅሙ በክብር እንዲያርፍና ምእመናን እንዲያከብሩት ይደረጋል፤

v ምእመናን በስሙ ሊሰየሙና ውሉደ እግዚአብሔር ሊባሉ ይችላሉ /በዓላት ምን? ለምን? እንዴት?፣ በዲ/ን ብርሃኑ አድማስ፣ 2005 ዓ.ም.፣ ገጽ 144-145/።

3. የሥርዓተ አምልኮ ቀኖና

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንፈጽመው ማንኛውም ዓይነት መንፈሳዊ ድርጊት የአምልኮ ባሕርይ አለው። ስናምን፣ ስንሰጥ፣ ስንቀበል ኹሉ አምልኮ ነው። ማንኛውንም ዓይነት ምሥጢር ስንፈጽም የእግዚአብሔር መኾናችንን ነው የምንገልጠው።

ያለ ሃይማኖት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን መቀበል አይቻልም። የእግዚአብሔር

ሀብት ከእግዚአብሔር ጋር በመኾን እንጂ እንደ ሲሞን መሠሪ የምንገዛው አይደለምና።

ሃይማኖት መታዘዝንም ይጨምራልና እንደ ቀኖና ዲያቆኑን፣ ቄሱን ወይም ጳጳሱን ማክበር ይጠበቅብናል። በጉድለት፣ በትዕቢት፣ በጭቅጭቅ የምንቀበል ከኾነ አለመታዘዝ ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ደናግላን ሳይኾኑ ተክሊል ካልተደረገልን ብለው ይጨቃጨቃሉ። በዚኽም ምሥጢረ ተክሊልን ሲፈጽሙ አምልኮተ እግዚአብሔር እየፈጸሙ እንደኾኑ ይረሳሉ። ከሥርዓተ አምልኮው ይልቅ በቤታቸው ስለሚሰቅሉት ፎቶ ይጨነቃሉ። ስለዚኽ ቀኖናና አምልኮ በእጅጉ የተቈራኙ መኾናቸውን ዐውቀን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምንፈጽማቸው መንፈሳዊ ድርጊቶች ላይ ልንጠነቀቅ ይገባናል።

4. ሥርዓተ ሲመትን የሚመለከት ቀኖና

በጥምቀት የተወለደ ኹሉ አገልጋይ ነው፤ "ያገለግሉኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ" እንዲል /ዘጸ.8፥1/። ይኸውም አሥራቱን ቀዳምያቱን የሚያወጣ፣ የሚታዘዝ ሕዝብ ይኾነኝ ዘንድ ማለት ነው። ከእነዚኽ ከተጠመቁት ተመርጠው የሚያገለግሉት ደግሞ ስዩማነ ካህናት (የአገልጋዮች መሪዎች) ይባላሉ። እነዚኽን ስዩማነ ካህናት ለመሾምም የራሱ የኾነ መስፈርት አለው። ይኽን መስፈርት ሳያሟላ ማንም ራሱን ሊሾም አይችልም። ከ12 ቱ ሐዋርያት አንዱ ይሁዳ ሲጐድል ሐዋርያት በይሁዳ ፈንታ ሌላ አንድን ሐዋርያ ለመሾም ሲጾሙ፣ ሲጸልዩ፣ ዕጣ ሲጥሉ፣ እጅግ ተጨንቀው ይኽን ኹሉ ሲያደርጉ ማየታችን ኹሉም ሰው ሐዋርያ እንዳልኾነ የሚያስረዳ ነው። በሌላ አገላለጽ አንድን ክርስቲያን ስዩመ ካህን ለማድረግ የራሱ መስፈርት እንዳለው የሚያስገነዝብ ነው።

በአጠቃላይ ቀኖና እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም፡-

1. የፍላጐት ልዩነት በሰዎች መካከል አይቀሬ ነው። እነዚኽን ሰዎች ወደ ስምምነት ለማምጣት ደግሞ የግድ ሕግ ያስፈልጋል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ አለመስማማቶችን የሚፈታ ነው።

2. በሰውነታችን ውስጥ ያሉት ብልቶች የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። ብዙዎች ቢኾኑም አንድ ሰውነት ናቸው። ብዙዎች ኾነው ሳለ የአንድ ሰውነት አባል ኾነው መቀጠል የሚችሉት ግን እጅ የእግርን፣ ዓይን የዦሮን ሥራ ልሥራ እስካላለች ድረስ ብቻ ነው። እንዲኽ ሕገ ተፈጥሮን ጥሶ መዘበራረቅ ካለ ሰውነት እንደ ሰውነት መቀጠል አይችልም። ልክ እንደዚኹ እኛ ክርስቲያኖችም ብዙዎች ብንኾንም የአንድ ክርስቶስ ብልቶች ነን። የአንድ ክርስቶስ ብልቶች ኾነን የምንቀጥለው ግን ካህኑ የክህነቱን ምእመናንም የምእመናንን ሥራ የሠራን እንደኾነ ብቻ ነው። አንዱ ምእመን ተነሥቶ የካህኑን ሥራ ልሥራ ቢል የቤተ ክርስቲያን አንድነት ሊጠበቅ አይችልም። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ይኽ አንድነት እንዲኖር ይረዳል።

3. ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነታችን መብታችንና ግዴታችንን ለይቶ የሚነግረን ነው። ለምሳሌ አንድ ምእመን ዐሥራት በኵራት የማውጣት ግዴታ አለበት። ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መገዛት አለበት። ይኽን ሳያደርግ ቀርቶ ከቤተ ክርስቲያን መጥቶ ምሥጢራትን ልፈጽም ቢል ተቀባይነት የለውም። የቤተ ክርስቲያን ሕግስ ይቅርና የትራፊክ ሕግም ጥቅሙ ብዙ ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

Rodas Tadese Abebe

አዘጋጅ መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የዶግማ መምህር (2005 ዓ.ም)

3/ ዶግማ (Dogma)

ዶግማ "dokein" (ዶኬይን) ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲኾን በነጠላ ፍቺው "አመለካከት፣ እምነት" ማለት ሲኾን በጥንት ጸሐፍት ዘንድ ለአንድ ሰው እውነት የመሰለው ሐሳብ አመለካከት ወይም የፍልስፍና የእምነት ሕገጋትና መሠረታዊ መመሪያ ተደርጎ ሲወሰድ በተለይ ተለይቶ ለታወቀ የፈላስፎች ትምህርት ቤት የተለየ ፍልስፍናዊ ሕገጋትን ሲያመላክት አልፎ አልፎ ደግሞ የመንግሥትን ትእዛዝና ዐዋጅን ያመላክት ነበር ።

በመጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ሥፍራ ላይ በተለይ በግሪክኛ በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ዶግማ የሚለው ቃል ሲገኝ በግእዝና በዐማርኛ በተተረጐመው መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ "ትእዛዝ፣ አዋጅ" ይለዋል (አስ 3፥3፤ ሉቃ 2፥1፤ የሐዋ 16፥4፤ 17፥7፤ ኤፌ 2፥15)።

በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትንታኔ ዶግማ ማለት በእግዚአብሔር ለሰዎች የተገለጸ እውነት ሲኾን ይኸም መገለጽ ለእኛ በቅዱሳን ሐዋርያት በኩል በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱስ ትውፊት የተላለፈልን የእምነት አስተምህሮ ነው፤ ይኸም በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ለአማኞች የሚታወጅ የሚደነገግ መቼም ቢኾን ሊለወጥ የማይችል እውነተኛ የሃይማኖት ትምህርት ነው፤

ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጊዜው እንደ ልዩ ልዩ ኹናቴው ሲለዋወጥና ሲሻሻል የክርስትና ሃይማኖታዊ ጽሑፎች (የነገረ እግዚአብሔር አስተምህሮዎች) ወይም የእምነት መግለጫዎች የኾኑ የየእምነት ትምህርቶች ግን ከቅዱስ መጽሐፍና ከቅዱስ ትውፊት የወጡ በቅዱስ ሲኖዶስ የጸደቁ እውነቶች ስለኾኑ በምንም ምክንያት መቼም ቢኾን ሊለወጡ ከቶ አይችሉም ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ቀጥ ያለው እምነቷን በዶግማ ለልጆቿ ስታስተላልፍ የስሕተት አስተምህሮም ቢነሣ እንኳን ትክክለኛውን የሃይማኖት ትምህርት በዶግማ ትገልጻለች፤ ይኽም እንግዳ ነገር ሳይኾን ከጥንት ከሐዋርያት ሲያያዝ የመጣ ሲኾን ለምሳሌ በሐዋ 15 ላይ እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው ለወንድሞችን የተሳሳተ ትምህርት ላስተማሩ ከይሁዳ ለመጡት ሰዎች ሐዋርያት ተሰብስበው "ያላዘዝናቸው ሰዎች ከእኛ ወጥተው ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ስለ ሰማን ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሆነን ፈቀድን፤ ራሳቸውም ደግሞ በቃላቸው ያንኑ ይነግሩአችሁ ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል ለጣዖት ከተሠዋ፥ ከደምም፥ ከታነቀም፥ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ ጤና ይስጣችሁ" በማለት የወሰኑትን የእምነት መግለጫ

ለሕዝቡ በደብዳቤ አስተላልፈዋል።

ዶግማን ቤተ ክርስቲያን እንደምታስምረው አድርጎ መቀበል፣ መጠበቅና አክብሮ መያዝ ለኹሉም የእምነት ተከታይ ግዴታ ሲኾን የቤተ ክርስቲያኒቱን የዶግማ ትምህርትን መቃወም ከጉባኤው በውግዘት የሚያስለይ ነው (ገላ 1፥8-9፤ 1 ጢሞ 1፥19-20) ፤ በክርስትና የዶግማ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን የሚተነተኑ በቤተ ክርስቲያኗ መጻሕፍትና ጉባኤ ለምእመናን የሚገለጹ ሲኾን እነዚኽም የዶግማ ትምህርቶች ሰውን ለድኅነት የሚያዘጋጁ ወደ እግዚአብሔር የሚመሩ እንደኾኑ ይታመንባቸዋል፤ የተለያዩ እምነቶች የራሳቸውን ዶግማ የሚያጸኑበት መመሪያ ሲኖራቸው ዐምስቱ አኀት አብያተ ክርስቲያናት ማለትም (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ፣ የሶርያ ኦርቶዶክስ፣ የአርሜኒያ ሐዋርያዊት ቤ/ክ፣ የሕንድ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ) የዶግማ ትምህርታቸው መሠረቱን በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱስ ትውፊት ላይ አድርጎ በሦስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ማለት በጉባኤ ኒቅያ፣ በጉባኤ ቊስጥንጥንያና በጉባኤ ኤፌሶን የተወሰኑ ውሳኔያትን ያጠቃልላል።

ህልዎተ እግዚአብሔር

የእግዚአብሔር ህላዌ ፈጽሞ ሊመረመር እንደማይችል መጽሐፍ ቅዱስና ምሥራቃውያን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በስፋት አስተምረዋል፤ ለምሥራቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ባሕርየ እግዚአብሔር ከመመርመር የራቀና የሰው ልጅም ዕውቀቱ ውሱንና ፍጹምነት የሌለው ስለኾነ እግዚአብሔር በገለጸውና ራሱን በቅዱሳት መጻሕፍት በሥነ ፍጥረት መጠን

በገለጸው መጠን እንደ እግዚአብሔርነቱን ዐውቆ ሊያመልከው እንጂ በመራቀቅ፣ በመጠበብ፣ በፍልስፍና ባሕርዩን ሊመረምረውና መጠኑ ይኽን ያኽላል፣ መልኩ ይኽን ይመስላል ብሎ ልክና መጠን ሊያወጣለት እንደማይችል አስተምረዋል።

ህላዌ እግዚአብሔር ስለአለመመርመሩ የመጽሐፍ ቅዱስና የአበው ምስክርነት

“የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ? ርዝመቱ ከምድር ይልቅ ይረዝማል፥ ከባሕርም ይልቅ ይሰፋል” (ኢዮ 11፥7-9)

“ደመና ጭጋግም በዙሪያው ናቸው ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው” (መዝ 97፥2)

“እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል” (ዮሐ 4፥24)

“የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው? ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን” (ሮሜ 11፥ 33-36)

“ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ

ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን" (1 ጢሞ 1፥17)

"ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ፥ ያሳያል እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን" (1 ጢሞ 6፥15-16)

"አልቦ ዘረከቦ ወአልቦ ዘይረክበከ ወአልቦ ዘየአምረከ ወአልቦ ዘይክል ርእዮተከ ክዱን ብከ ዕበይከ ወሥውር ብከ ኀይልከ ለሊከ ብከ ተከደንከ" (ያገኘኽ የለም ሊያገኝኽም የሚችል የለም አንተን ማወቅና በባህሪህ ማየት የሚችል የለም፤ አንተ ኀይልኽ የተከደነ ጌትነትኽ የተሰወረ ነው ማንም ሊያይኽ ወይም ሊያገኝኽ አይችልም) ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ቊ 5-8

""ሥውር ውእቱ ዘኢይረክብዎ በሕሊና ወምጡቅ ውእቱ ዘኢይጤይቅዎ በልቡና ነዋህ ውእቱ ዘኢይበጽሕዎ አንስርት ቀላይ ውእቱ ዘኢይጸብትዎ ዓሣት" (ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ቊ 6)

"ለእመ ተጋብኡ ኀቡረ መላእክት ወሊቃነ መላእክት በበዘመዶሙ ወበበሥርዐቶሙ ዘምስለ ኵሎሙ ፍጡራን አሐተኔ ኢይክሉ ይርከቡ ኀዳጠ እምአእምሮተ ኀላዌሁ ለእግዚአብሔር" (መላእክትና የመላእክት አለቆች ኹሉ በየወገናቸው በየሥርዐታቸው ፍጡራን ከኾኑት ኹሉ ጋር አንድ ላይ በአንድነት ቢሰበሰቡ የእግዚአብሔርን ህላዌ በጥቂቱ እንኳ ሊያገኙት አይችሉም) (ሃይ. አበው ዘባስልዮስ ክፍል 4 ቊጥር 14)

"እፎኑመ ነአምር ምስጢሮ ለፈጣሪ ዘኢተፈጥረ ዘይትሌዐል ኵሎ

ሕሊናተ...ሰቦሰ ክህልነ ኅሢሦቶ ወእምአመርናሁ እምአሕፀፅነ ዘኅየ ዕበዮ ለመንፈሳዊ" (ያልተፈጠረና ከሐሳቦች ኹሉም በላይ ከፍ ከፍ ላለ ፈጣሪ እኛ ምስጢሩን እናውቅ ዘንድ እንዴት እንችላለን?...በምርመራችን ተመራምረን ፈልገን ብናውቀው ኖሮ ከወዲያ ያለውን የመንፈሳዊን ፍጹምነትና ታላቅነት ጒድለት እንዳለው አድርገን ባስገመትነው ነበር) (ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ክፍል 2 ቍ 16)

"ለእመ ሐተትነ ዕበዮ በነገር እስመ ሕሊና ይደክም ወየሐጽር እምአእምሮተ መለኮቱ ዘኢይትረከብ፤ ወቃልሂ ኢይክል ይክሥት ዘኢክህለ ነጽሮተ ሕሊና...ቦኑ ይትከሀለነ ንጠይቅ ስፍሐ ሰማይ ወዕመቀ ቀላይ እስመ ኢንክል ንጠይቅ ኅዳጠ እምፍጡራን፤ እፎኑመ ይትከሀለነ ንብጻሕ ኀበ አእምሮተ እግዚአብሔር፤ እመሰ ይርኅቆ ለሕሊናነ አእምሮተ ምግባራት ዘንኔጽሮሙ ወኢንክል ተናግሮ ዘከመ ድልወቶሙ፤ እፎኑመ ንትበሀል ለተናግሮ ዘኢያእመርነ" (ታላቅነቱን በነገር ብንመረምር የማይደረስበት መለኮቱን ከማወቅ ሕሊና ይደክማል ያጥራልም፤ ቃልም ሕሊና ያላየውን ሊገልጠው አይችልም...በውኑ የሰማይ ስፋትን የውቅያኖስ ጥልቀትን ለመረዳት ይቻለን ይኾን? ታዲያ ከፍጡራን በጥቂቱ ለመረዳት የሚሳነን ከሆነ እግዚአብሔርን ወደማወቅ እንዴት እንደርሳለን?፤ የምናያቸው ሥራዎች ለማወቅ ለሕሊናችን የሚርቀው ከሆነ ስለ እነርሱ እንደሚገባ ለመናገር የሚሳነን ከሆነ፤ ያላወቅነውን ለመናገር እንዴት እንደፍራለን?) ቅዱስ ባስልዮስ ሃይ.አበ ክፍል 4 ቍ 3፥12

"እስመ ኢይትከሀሎ ለልሳን ይንብብ በእንቲኣሁ ከመ ድልወቱ፤ ወሕሊናሂ ኢይክል ሰሚያቶ፤ ኅድግሰ ልሣነ ሕሊና ልብኒ ዘይከብር እምኔሁ ኢይጤይቅ

ምንተኒ እምኔሁ እስመ ንኄሊ በእንቲኣሁ በብዙኀ ሐተታ ሎቱ ስብሐት ወንስዕን ፈክሮ” (ስለ እግዚአብሔር ህላዌ አንደበት ሊናገር አይቻለውም የልብ ሐሳብም ሊሰማ እንኳ አይቻለውም የአንደበትን ማለትም የልሳንን ኹኔታ ተወውና፤ ከእርሱ (ከልሳን) የከበረ የልብ ኅሊና ሐሳብ እንኳ ከርሱ መረዳት ያቅተዋል ክብር ምስጋና ይኹንለትና ስለ እርሱ እንመረምራለን ዳሩ ግን መተርጐሙ ያቅተናል) ድርሳን ዘዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሳን 2፤ ገጽ 24

“እስመ እግዚአብሔር ኢይትረከብ በሕሊና ዕጓለ እመሕያው ወሕሊና እጓለ እመሕያው ኢይረክብ መለኮተ፤ ወህላዌ መለኮት ርኁቅ እምሕሊና እጓለ እመ ሕያው ወይትሌዓዐል ኩሎ ሕሊናተ ፈድፋደ” (እግዚአብሔር በሰው ልጅ ሐሳብ አይገኝም የሰው አስተሳሰብ መለኮትንና ሕላዌ መለኮትን ሊያገኝ አይችልም፤ የመለኮት ህላዌ ከሰው ልጅ አስተሳሰብ የራቀ ነውና፤ ከሐሳቦች ኹሉም ይልቅ በጣም ከፍ ያለ ነውና) ሃይ. አበ ዘቴዎዶጦስ ክፍል 1 ቍ 2፤ ገጽ 171

“ኦ ብእሲ በመኑ ታስተማስሎ ለዘኢይትማሰልዎ ፍጡራን ወዘከመ እፎ ትሔልዮ ለዘኢይትሄለይ፤ ኢይደሉ ያስተዐርይዎ በፍጡራን በመኑሂ፤ ኢበመብረቅ በእንተ ግርማሁ፤ ወኢበፀሐይ በእንተ ልዑል ብርሃኑ፤ ኢበሰማይ በእንተ ልዕልናሁ፤ ወኢበምድር በእንተ ራኀቡ፤ ወኢበባሕር በእንተ ዕመቂ፤ ወኢበእሳት በእንተ ዋዕዩ፤ ኢበነፋስ በእንተ ርቀቱ ወፍጥነቱ፤ ወኢበምንትኒ ኢይትረከብ በእንተ ጥያቄ መለኮቱ ለአምላከ ጽድቅ፤ ኢተውህበ ለፍጥረት ያእምር መነሂ ወመኑሂ፤ ወበእንተዝኬ ኢይደሉ ንኅሥሥ ክዋኔሁ ለዘኢይትዐወቅ ኩነቱ” (ሰው ሆይ ፍጥረታት

ለማይመስሉት በምን ታመሳስለዋለኽ? የማይታሰበውንስ እንዴት አድርገኽ ልታስበው ትቃጣለኽ? በፍጡራን ሊያስተካክሉት የሚገባ አይደለም፤ በምንም በማናቸውም ስለ ግርማው በመብረቅ፤ ከፍተኛ ስለኾነው ብርሃኑ በፀሓይ፤ ስለልዕልናው በሰማይ፤ ስለ ስፋቱ በምድር፤ ስለጥልቀቱ በባሕር፤ ስለማቃጠሉ በእሳት፤ ስለርቀቱና ስለፍጥነቱ በነፋስ ወይም በማናቸውም ቢኾን የእውነት አምላክ መለኮትነት ሊያስረዳ ይችላል ተብሎ አይታሰብም፤ ይኽ ለፍጥረት ያልተሰጠውና በማናቸውም ኹኔታውን ለመረዳት አይቻልም ስለዚኽም ኹኔታውን ለመመርመር አይቻልም) ርቱዐ ሃይማኖት ምዕ 3 ክፍል 2 ምዕ 22፥2

ኾኖም ግን አንዳንድ የምዕራብ የነገረ እግዚአብሔር መርማሪዎች ፍልስፍናዊ አካኼድን በመከተል ህላዌ እግዚአብሔርን ለመመርመር ሙከራ አድርገዋል፤ ከነዚኽ መካከል ለምሳሌ የካቶሊክ መምህር የኾነው ቶማስ አኪውናስ አንዱ ሲኾን “ሱማ ቲዎሎጂካ” በሚባል ሥራው “መንገዶች” በሚል የሰየመው ህልዎተ እግዚአብሔርን ለማሳወቅ ዐምስት ማረጋገጫ ሲያቀርብ፤ እንደርሱ ምልከታ ስለእግዚአብሔር ሐልዎት በመለኮታዊ መገለጥና በሰዎች ዕውቀት ዕውነታው ሊታወቅ ይችላል ብሏል፤ አኪውናስ የነበረበት ጊዜ የአሪስቶትል ፍልስፍናዊ ትምህርት ዕውቅና ያገኘበት ስለነበር ይኽነን መሠረት አድርጎ አስተምሯል ። ከርሱ በኋላም ብዙዎች ከአኪውናስ ጽንሰ ሐሳቦች በመነሣት በመነሣት ህላዌ እግዚአብሔርን ለማወቅ ከፍተኛ ሙከራን አድርገዋል፤ እንደ ምሥራቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አስተምህሮ ደግሞ እግዚአብሔር በፍልስፍና የሚደረስበት ቢኾን የሃይማኖት ትምህርት ኹሉ የፍልስፍና ትምህርት በኾነ

ነበር፤ ሃይማኖትም ራሱ ፍልስፍና በኾነ ነበር፤ እግዚአብሔርም ፈጣሪ መኾኑ ቀርቶ እንደ ፍጡር ወደፊት የሚደረስበት በኾነ ነበር ይላሉ።

[ከዚኽ በመቀጠል በክፍል ውይይት ውስጥ ከደቀ መዛሙርት ጋራ ህልዎተ እግዚአብሔርን ለማሳወቅ አኲውናስ የተጠቀማቸውን ዐምስት መንገዶች ዳግመኛም በተለያዩ ምሁራን የተጠቀሱ 20 ሌሎች መንገዶችና በተለያዩ ተመራማሪዎች የተተነተኑ መቶ መንገዶችን “Hundreds of Proofs of God’s Existence” በስፋት ስናይ ያላቸውንም ክፍተት የምንገመግመው ይኾናል።]

Diacon Ankets Tekola

ውዶቼ በቸርነቱ እኛ ቀድሰን እናንተም አስቀድሳችሁ ግን በግቡ ተቀድሰን ባዘጋጀልን ዳስ ውስጥ ከትመናል ሁሉን በፈቃዱ እድናከናውን ያደለን አምላክ የተመሰገነ ይሁን።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትውፊታዊ ስርዓት በሚገባ ለማወቅ እንጣር። ማወቅ ወላጅ ደግም ማንበብ ነውና አሁን ከምታንቡት በላይ አንባቢ ሁኑ።

ግና ንግግሬ የቀለም አልባ ሰው ከሆነባችሁ በጣም ይቅርታ። "የምታነቡትን ዕወቁ የቤተ ክርስቲያንን የክብር ስም ይዘው መጻሐፎቻቸው ትችት ብቻ የሆኑ አሉና። ግና እኛ የሚያስፈልገን የትች መጻሐፍ ሳይሆን የወንጌል፣የቅዳሴው፣የሃይማኖተ አበው፣የግብረ ሕማማቱ፣የአብጥሊሱ፣

ወዘተ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉ የአድምታ መጸሕፍት እናንብብ።እዲሁም ታሪክ መጋቢ መጸሐፍት፣ የቅዱሳን ምልጃን እያነባን እድናነባቸው የሚያደርጉ መጸሐፍት አሉና እናንብብ።

የእውነት እንኑር ። ሌላው የምናውቀውም የማናውቀውም የመጸሐፍ ቅዱስ ቃላትን የግል ወግ ማውጊያ እናደርጋቸለን።

ለምሳሌ "መሐልየ መሐልይ" ያለውን ውስጠ ሚስጢር ባለመረዳት ለስጋዊ ስሜት መግለጫ የሚደረጉበት ሁኔታ አለ። በዕውነት ነው የምላችሁ "ጦር የጠፋለት ሰው" እዲጸልየው የታዘዘውን ይህን የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል ብታነቡት ምስጢሩ ራሱ ዓይኖቻችሁ በእንባ ይምላሉ።

ተፈጥሮ በራሱ በ2 ነገሮች የተመላች ነች። ሀዘን ደስታ፣ገነት ሲኦል፣ የዕውነት አገልጋይ የደምዝ አገልጋይ፣ መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ርኩስ 'ወዘተ ለፈጣሪ ምቹ ሆነን የዕውነት እንኑር።

አሁን የፍጻሜው ጊዜ ነው አብዝተን የማንጸልይበት አንድም ምክንያት የለምና እንጸልይ"ስለ ሐገር ፣ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮች ፣ሰላም፣ ሎጥ ያዘነበት ግብርም እየገሰገሰ ነውና አቤት እንበል አረ ስንቱ።

እየጸለይን የዕውነተ ዕንኑር። ሰላም

Ethiopian Orthodox Tewahdo Books

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ መጻሕፍት አንባብያን ቡድን

4/ ትውፊትና ዕድገት

(ትውፊት፡- ውርስ፣ ቅብብል ማለት ነው። ይኸውም አንድ ትውልድ ከርሱ በፊት ከነበሩት የሚወርሰው፣ የሚያገኘው፣ የሚቀበለው ነገር ነው።)

ብዙ ሰዎች ሁል ጊዜ የቀደሙትን ከተመለከትን ዕድገታችን ፤ የትውልዱም የፈጠራ ችሎታ ይቋረጣል ብለው ሥጋታቸውን ይገልጣሉ። ነገር ግን ትውፊት ዕድገትን አይገድብም እንዲያውም ዕድገቱ የተስተካከለ እነዲሆን ያደርገዋል።

ማደግ ማለት የራስን ትቶ የሌላውን ብቻ መቀበል አይደለም። የራስ የሆነውን በአግባቡ መጠቀም ማለት ነው እንጂ ዕድገታችን እንጀራን አጥፍተን ፓስታ ብቻ ለምን አንበላም? የሐበሻ ቀሚሱን አሳድደን ለምን ዕርቃንን የሚያጋልጠውን አንለብስም? የዘመን አቆጣጠራችን ይቅርና የአውሮፓ ቀመር ይተካ። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ተጥሎ፤ የነሞዛርት ቅኝት ይምጣልን ዓይነት ከሆነ ጉዞዋችን ወደ ማደግ ሳይሆን አንገትን ቆርጦ ለፀጉር አበጣጠር የመጨነቅ ያህል ነው።

የራሳችን የሆነውን ወደን፣ አክብረን የበለጠ የሚያድግበትን መንገድ መፈለግ ከሆነ ያ ዕድገት ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

(ቤተክርስቲያንህን ዕወቅ፣ አንደኛ መጽሐፍ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 1988 ዓ.ም፣ ገጽ 10)

## Mekrez Ze Tewahdo

### 5/ ዶግማ እና ቀኖና

ውድ የመቅረዝ ተከታታዮች! እንዴት አላችሁ? ትምህርተ ሃይማኖት በሚል

ርእስ መማማር ከዠመርን የዛሬ ስድስተኛው ክፍል ነው። ባለፉት አምስት ተከታታይ ትምህርቶች የሃይማኖት ትርጕም፣ ሃይማኖት ያላቸው ፍጥረታት፣ የሃይማኖት አስፈላጊነት፣ ኦርቶዶክስና ተዋሕዶ ስለሚሉ አገላለጾች፣ ስለ ነገረ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ቅዱስ ትውፊት እንዲኹም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ኦርቶዶክሳዊ አረዳድ ተመልክተናል። ለዛሬ ደግሞ ከመግቢያው የመጨረሻ ስለኾነው ስለ ዶግማና ቀኖና እንማማራለን። ቢቻላችኁ ለማንበብ በቂ ጊዜ ሰጥታችኁና ተረጋግታችኁ ብታነቡት መልካም ነው። እግዚአብሔር ዓይነ ልቡናችንን ያብራልን። አሜን!!!

በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ትምህርት በኹለት ትምህርቶች የሚጠቃለል ነው። ዶግማ እና ቀኖና ተብሎ።

1. ዶግማ

ዶከይን ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲኾን በጥሬው አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ አዋጅ ማለት ቢኾንም በምሥጢራዊ ማለትም በቤተ ክርስቲያናዊ ትርጓሜው ግን ሃይማኖት (የእምነት መሠረት) ማለት ነው። በመኾኑም ዶግማ የተደነገገ ሳይኾን የተገለጠ ነው። መገኛውም እግዚአብሔር ነው። ከሰው ሊፈጠር አይችልም። ከእግዚአብሔር የተሰጠ እውነት ነው። በማኛኛውም አካል (በሲኖዶስም ጭምር)፣ በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛውም ኹኔታ (በሞትም በሕይወትም) የማይለወጥ ማንነት አለው።

ዶግማ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርተ ሃይማኖት ነው ብለናል። ስለ ቅድስት ሥላሴ፣ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ (ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መኾኑን፣ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተጸንሶ

በድንግልና እንደተወለደ፣ እንደ ተሰቀለ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ፣ ዳግመኛ በክበበ ትስብእት እንደሚመጣ)፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ስለ ምሥጢረ ቁርባን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያንና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ክብረ ድንግል ማርያምና ክብረ ቅዱሳን የምንማው እንጂ ማናችንም ልናሻሽለው አንችልም። እንኳንስ አንድ ግለሰብ ይቅርና ሲኖዶስም ቢኾን አለመለወጡን፣ አለመፋለሱን ይመረምራል እንጂ መጨመር ወይም መቀነስ አይችልም። ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- “ነገር ግን (ሐሳባችንን ቀይረን) እኛ ብንኾን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችኁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን የሚሰብክላችኁ የተረገመ ይኹን” ያለውም ስለዚኹ ነው /ገላ.1፥8/።

2. ቀኖና

ቀኖና ማለት ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ፍርድ፣ ቅጣት፣ መጠን፣ ልክ ማለት ነው /ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ገጽ 799/። በግሪኩ ካኖን ሲኾን በዕብራይስጡ ቃኒህ ይሉታል። ይኸውም አንድን ነገር ለመለካት፣ ለመመዘን፣ ትክክል መኾኑንና አለመኾኑን ለመለየት፣ መጠኑን ለማወቅ የሚያገለግል መለኪያ ወይም መስፈርት ነው።

ማኅበረ ሰብእ እስካለ ድረስ ሕግ አለ። ሕግ እንዲኖር የኹለት ሰዎች በአንድ ላይ መኖር በቂ ነውና። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ “አሐቲ ጉባኤ” እንዲል የምእመናን ስብስብ ስለኾነች የራሷ ሕግ አላት። አባቶች “ያልተገራ ፈረስ የባለቤቱን ጥርስ ይሰብራል” እንደሚሉት ይኽ የምእመናን ስብስብ ሰላማዊ እንዲኾን የሚያደርገው የቤተ ክርስቲያን ሕግ ወይም

ሥርዓትም ቀኖና ይባላል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው ሕግ ኹለት ዓይነት ነው፤ ተፈጥሮአዊ ሕግና የስምምነት ሕግ። የተፈጥሮ ሕግ የምንለው የእግዚአብሔርን ሕግ ነው። ሰዎች ይኽን የእግዚአብሔር ሕግ ሊለውጡት አይችሉም። ለምሳሌ ወንድ ከሴት ጋር መጋባት አምላካዊ ሕግ ነው። ግብረ ሰዶማዊነትም ይኽን የተፈጥሮ ሕግ የሚቃረን ነው። ፈረስና አህያ ተዳቅለው በቅሎን ይወልዳሉ። ነገር ግን በቅሎ ራሷን መተካት አለመቻሏ ከሕገ ተፈጥሮ ውጪ የተወለደች መኾኗን ነው የሚነግረን። ጦጣና ዝንጀሮ ተዳቅለው የሚወልዷቸው እንስሳትም አሉ። ነገር ግን ልክ እንደ በቅሎ ራሳቸውን መተካት አይችሉም። ለምን? ስንልም ከሕገ ተፈጥሮ ማለትም ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ የተወለዱ ናቸውና። ስለዚኽ ተፈጥሮአዊ ሕግጋትን ተቃርነን የምናደርጋቸው ነገሮች ትርፉ ድካምና በራስ ላይ ጉዳትን መጨመር ብቻ ነው የሚኾነው።

ሙሉውን ለማንበብ ከስር ያለውን ማስፈንጠሪያ ይጫኑ…

Gebre Egziabher Kide

6/ ስለ ቀኖና ምን ያኽል ግንዛቤ አለዎት?

- የዶግማና የቀኖና ልዩነቱ ምንድነው?
- ቀኖና ባይኖር ምንድነው ጉዳቱ?

- የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ዓላማ ምንድነው?
- "ይኼ እኮ ቀኖና ነው፤ ባናደርገውም ምንም ችግር የለውም" የሚለው ብሒል ምን ያኽል ክርስቲያናዊ ነው?
- በኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንድ ገዳማት ላይ ሴቶች አይገቡም የሚባልበት ሚሥጥሩ ምንድነው?
- ቅዱሳን አበው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ለመለየት የተጠቀሙበት መሥፈርት ምንድነው? የሐዲስ ኪዳንንስ?
- ለመኾኑ አንድ መጽሐፍ (በግለ ሰዎች የሚዘጋጁትም ጭምር) ኦርቶዶክሳዊ መኾኑንና አለመኾኑን እንዴት እንለየዋለን?
- አንድን ቅዱስ ቅዱስ ለመባል መለኪያ አለውን?

በትምህርተ ሃይማኖት ክፍል ስድስት ትምህርታችን እነዚኽንና እነዚኽን የመሰሉ ትምህርቶች ተካተዉበታል። ይከታተሉን።

ትምህርተ ሃይማኖት (ክፍል ስድስት)

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

7/ ዶግማ እና ቀኖና.....

የእግዚአብሔር ቤተሰቦች! እንዴት አላችኍ? ትምህርተ ሃይማኖት በሚል ርእስመማማር ከዠመርን የዛሬ ስድስተኛው ክፍል ነው። ባለፉት አምስት ተከታታይ ትምህርቶች የሃይማኖት ትርጒም፣ ሃይማኖት ያላቸው ፍጥረታት፣የሃይማኖት አስፈላጊነት፣ ኦርቶዶክስና ተዋሕዶ ስለሚሉ

አገላለጾች፣ ስለ ነገረ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ቅዱስ ትውፊት እንዲኹም ስለመጽሐፍ ቅዱስ ኦርቶዶክሳዊ አረዳድ ተመልክተናል። ለዛሬ ደግሞ ከመግቢያው የመጨረሻ ስለኾነው ስለ ዶግማና ቀኖና እንማማራለን። ቢቻላችት ለማንበብ በቂ ጊዜ ሰጥታችኁና ተረጋግታችኁ ብታነቡት መልካም ነው። እግዚአብሔር ዓይነ ልቡናችንን ያብራልን። አሜን!!!

በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ትምህርት በኹለትትምህርቶች የሚጠቃለል ነው። ዶግማ እና ቀኖና ተብሎ።

1. ዶግማ

ዶከይን ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲኾን በጥሬውአመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ አዋጅ ማለት ቢኾንም በምሥጢራዊ ማለትም በቤተ ክርስቲያናዊ ትርጓሜው ግን ሃይማኖት (የእምነት መሠረት)ማለት ነው። በመኾኑም ዶግማ የተደነገገ ሳይኾን የተገለጠ ነው። መገኛውም እግዚአብሔር ነው። ከሰው ሊፈጠር አይችልም። ከእግዚአብሔርየተሰጠ እውነት ነው። በማኝኛውም አካል (በሲኖዶስም ጭምር)፣ በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛውም ኹኔታ (በሞትም በሕይወትም) የማይለወጥማንነት አለው።

ዶግማ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርተ ሃይማኖት ነው ብለናል። ስለ ቅድስትሥላሴ፣ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ (ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መኾኑን፣ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተጸንሶበድንግልና እንደተወለደ፣ እንደ ተሰቀለ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ፣ ዳግመኛ በክበበ ትስብእት እንደሚመጣ)፣ ስለመንፈስ ቅዱስ፣ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ስለ ምሥጢረ ቁርባን፣ ስለ ቤተ

ክርስቲያንና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ክብረ ድንግልማርያምና ክብረ ቅዱሳን የምንማው እንጂ ማናችንም ልናሻሽለው አንችልም። እንኳንስ አንድ ግለሰብ ይቅርና ሲኖዶስም ቢኾን አለመለወጡን፣አለመፋለሱን ይመረምራል እንጂ መጨመር ወይም መቀነስ አይችልም። ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ “ነገር ግን (ሐሳባችንን ቀይረን)እኛ ብንኾን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችኁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን የሚሰብክላችኁ የተረገመ ይኹን” ያለውም ስለዚኹ ነው/ገላ.1፥8/።

2. ቀኖና

ቀኖና ማለት ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ፍርድ፣ ቅጣት፣ መጠን፣ ልክ ማለት ነው/ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ መጽሐፈሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ ገጽ 799/። በግሪኩ ካኖን ሲኾን በዕብራይስጡ ቃኒሀ ይሉታል። ይኸውምአንድን ነገር ለመለካት፣ ለመመዘን፣ ትክክል መኾኑንና አለመኾኑን ለመለየት፣ መጠኑን ለማወቅ የሚያገለግል መለኪያ ወይም መስፈርትነው።

ማኅበረ ሰብእ እስካለ ድረስ ሕግ አለ። ሕግ እንዲኖር የኹለት ሰዎች በአንድላይ መኖር በቂ ነውና። ቤተ ክርስቲያን ደግሞ “አሐቲ ጉባኤ” እንዲል የምእመናን ስብስብ ስለኾነች የራሷ ሕግ አላት። አባቶች“ያልተገራ ፈረስ የባለቤቱን ጥርስ ይሰብራል” እንደሚሉት ይኽ የምእመናን ስብስብ ሰላማዊ እንዲኾን የሚያደርገው የቤተ ክርስቲያንሕግ ወይም ሥርዓትም ቀኖና ይባላል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው ሕግ ኹለት ዓይነት ነው፤ ተፈጥሮአዊ ሕግናየስምምነት ሕግ። የተፈጥሮ ሕግ የምንለው የእግዚአብሔርን ሕግ

ነው። ሰዎች ይኽን የእግዚአብሔር ሕግ ሊለውጡት አይችሉም። ለምሳሌወንድ ከሴት ጋር መጋባት አምላካዊ ሕግ ነው። ግብረ ሰዶማዊነትም ይኽን የተፈጥሮ ሕግ የሚቃረን ነው። ፈረስና አህያ ተዳቅለውበቅሎን ይወልዳሉ። ነገር ግን በቅሎ ራሷን መተካት አለመቻሏ ከሕገ ተፈጥሮ ውጪ የተወለደች መኾኗን ነው የሚነግረን። ጦጣና ዝንጀሮተዳቅለው የሚወልዷቸው እንስሳትም አሉ። ነገር ግን ልክ እንደ በቅሎ ራሳቸውን መተካት አይችሉም። ለምን? ስንልም ከሕገ ተፈጥሮማለትም ከእግዚአብሔር ሕግ ውጪ የተወለዱ ናቸውና። ስለዚኽ ተፈጥሮአዊ ሕግጋትን ተቃርነን የምናደርጋቸው ነገሮች ትርፉ ድካምናበራስ ላይ ጉዳትን መጨመር ብቻ ነው የሚኾነው።

የስምምነት ሕግ የምንለው ደግሞ በፓርላማ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በቤተክርስቲያን ደግሞ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣውን ሕግ ማለታችን ነው። ምንም እንኳን የስምምነት ሕግ ብለን ብንጠራውም ቅዱስ ሲኖዶስንየሚመራው መንፈስ ቅዱስ ስለኾነ እንዲኹ የሰዎች ስምምነት ነው ብለን የምንወስደው ወይም ዝቅ አድርገን የምንመለከተው አይደለም። እነዚኽ ሕጎች ኹለት መሠረታዊ ጠባያት አሏቸው። ጥቅል ወይም ዝርዝር ሕጎች ሊኾኑ ይችላሉ።

የስምምነቱ ሕግጊዜያዊም ለረዥም ጊዜ የሚቈይም ሊኾን ይችላል። ለምሳሌ እግዚአብሔር በምሕረት ዓይን እንዲያየንና በቤተ ክርስቲያን እንዲኹም በዓለምላይ የተጋረጡትን ችግሮች እንዲያርቅ ቅዱስ ሲኖዶስ ለኹለት ሳምንት ጾምና ጸሎት ቢያውጅ ጊዜአዊ ሕግ (ቀኖና) ይባላል። በዓመትሰባት የአዋጅ አጽዋማት መኖራቸው ግን በሕይወት እስካለን ድረስ

የሚገዛን ቀኖና ነው።

የስምምነት ሕግ የተጻፈም ያልተጻፈም ሊኾን ይችላል። ያልተጻፈ መኾኑ ግንሕግ ከመኾን አይከለክለውም። ካልተጻፈ ተብሎ አይጣስም። እያንዳንዳችን የአንዳችንን ፍላጐት ለመጠበቅ ተፈጥረናልና /ዘፍ.4/።

ቀኖና ቤተ ክርስቲያን

ቀኖና የሚለው ቃል እንደ አኹኑ ለቤተ ክርስቲያንከማገልገሉ በፊት ሕዝቡ በማንኛውም የዕለት ተዕለት ሕይወቱ የሚዳኝበት ሕግን ያካተተ ነበር። ቤተ ክርስቲያናዊ (ክርስቶሳዊ ሕግ)እና ሕዝባዊ (ቄሳራዊ) ሕግ ተብሎ የተለየው በኋላ ነው /TheOxford Dictionary of the Christian Church, pp 277/። ቤተክርስቲያንም መዠመሪያ አከባቢ ላይ ቀኖና የሚለውን ቃል ስትጠቀም የመጻሕፍቶቿን ዝርዝር፣ የሥርዓተ አምልኮቷን አፈጻጸም፣ የምሥጢራተቤተ ክርስቲያንን አፈጻጸም፣ የአንድ ክርስቲያን ሥነ ምግባር ምን መምሰል እንዳለበት ለመግለጥ ነበር። ይኽ ቀኖና እንዲኖራት ምክንያትየኾናትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይከሰቱ የነበሩት አለመግባባቶች ናቸው። በተለይ አንዳንድ ከእምነትም ከምግባርም የሚወጡ ሰዎችሲገኙ ምእመናን ግራ እንዳይጋቡ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ይወጣ ነበር። እንደ ችግሩ መጠንም የሚወጣው ሕግ (ቀኖናው) ዳርቻው አጥቢያዊ፣ወይም ሀገረ ስብከታዊ፣ ወይም ሀገራዊ፣ ወይም ዓለማቀፋዊ ይዘት ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ ትንሽ ቆየት ብለን እንደምንመለስበትበጉባኤ ኒቅያ የተደነገጉት ቀኖናት ዓለማቀፋዊ ይዘት ያላቸው ቀኖናት ናቸው /Ibid/።

ቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊት ካልኾነች እውነተኛ አይደለችም።

የእግዚአብሔርንልጅ ማወቅ ብቻውን ትርጒም የለውም፤ አጋንንትም ያውቁታልና። ትርጒም የሚኖረው ስናምንና ስንጠመቅ ነው። ይቅርታ ሰላምን እንደሚሰጥይታወቃል፤ ይቅር ካላልን ግን ትርጒም የለውም። በሌላ አገላለጽ እምነታችንን የምናከናውንበት ዝርዝር ቀኖና ከሌለ እምነታችን ትርጒምአልባ ነው፤ ምክንያቱም ቀኖና “እምነታችንን እንዴት እንፈጽም?” ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ዝርዝር አፈጻጸም ነውና።

የቤተ ክርስቲያን ቀኖናት የተሰጡት በሐዋርያት ነው። ለሕዝቡ ያስተማሩትምእነርሱ ናቸው። በእነርሱ ወንበር የተቀመጡት ሊቃነ ጳጳሳትም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት ጊዜውን የዋጀ ቀኖና ይሠራሉ።

ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ከሌለ የሚሠለጥነው ዲያብሎሳዊ ሕግ ነው። የቀኖና ቤተክርስቲያን ዋና ዓላማም ሰዎችን ሥርዓት አስይዞ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖራቸው ማድርግ ነው። እንደ ምሳሌ ብንጠቅስ አርዮስንለመገሰፅ ቤተ ክርስቲያን 25 ዓመት ፈጅቶባታል። የኢትዮጵያ እስር ቤቶች እንኳን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ደብረ ሐይቅ (የግራኝመሐመድ ወንድም የታሰረበት)፣ ደብረ ዳሞ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ፣ ክብራን ገብርኤል፣ ግሸን ደብረ ከርቤ እና ሌሎች ታላላቅ ገዳማትነበሩ። ይኽ የኾነበት ዋና ምክንያትም የቀኖና ዓላማ ሰዎች እንዲታረሙ ማድረግ እንጂ ሰውን መቅጣት ስላልኾነ ነው። አጼ ቴዎድሮስአንድን ሌባ ያገኛሉ። ይዘዉም እጁን ይቈርጡታል። በዚያን ጊዜ የነበሩ ታላቁ ሊቅ አለቃ አካለ ወልድም በቅኔ አድርገው አጼ ቴዎድሮስንወረፏቸው። አለቃ አካለ ወልድ ይኽን ያደረጉበት ዋና ምክንያትም “ሰውዬው እጁ ስለተቈረጠ ከዚያ በኋላ መሥራት አይችልም፤ የሰውጥገኛ ነው የሚኾነው። ቀኖና ሊሰጠው ይገባ ነበር” ሲሉ ነው፤

እንደተናገርን የቀኖና ዓላማ ሰውን ማዳን እንጂ ሰውን መጉዳት ወይምጫና መፍጠር አይደለምና።

“ሕግ ከጽዮን ይወጣል” /ኢሳ.2፡3/ እንደተባለ የሕግ ምንጭ ቤተ ክርስቲያንነች። ሕግ አውጪ ብቻ ሳትኾን ሕግ ተርጓሚዋና ሕግ አስፈጻሚዋም ርሷ ራሷ ናት። ሕጓም ዓለምአቀፋዊ ዳርቻ አለው። ቤተ ክርስቲያንባለችበት ኹሉ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንም አለ። አትስረቅ፣ አትግደል፣... የሚሉት የቤተ ክርስቲያን ሕጎች ናቸው። በመኾኑም እነዚኽሕጎች በማንኛውም ቄሣራዊ ሥርዓት፣ በማንኛውም ዓይነት ቋንቋ፣ በማንኛውም ዓይነት ማኅበረ ሰብእ ውስጥ አሉ። የሥላሴ አጥር ዳርድንበር የለውምና የቤተ ክርስቲያን ሕግም ዳር ድንበር የለውም። ጾም የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው። አፈጻጸሙ ግን እንደየቦታውናእንደየሰዉ ኹናቴ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ በዓፋር የሚኖር ክርስቲያን እስከ ዘጠኝ ሰዓት ካልጾምኩ ካልነው በውኃ ጥም እንገድሏለን።አዲስ አበባ ላይ የሚኖረው ክርስቲያን ዓፋር ላይ እንደሚኖረው ክርስቲያን 4፡00 ሰዓት ላይ ውኃ ልጠጣ ቢል ግን የተለየ ምክንያትከሌለው በቀር ተቀባይነት የለውም። እንዲኽ ሲባል ግን እያንዳንዱ ሰው በራሱ ሕሊና ያለበትን ኹናቴ እያመዛዘነ በራሱ ውሳኔ የሚያደርገውነው ማለታችን አይደለም። እንዲኽ ዓይነት ለየት ያለ ቀኖና (Exceptional Canon) የሚያወጣው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጋዊአካል ብቻ ነውና “ይኼ እኮ ቀኖና ነው፤ ባናደርገውም ምንም ችግር የለውም” ከሚለው ግላዊ አስተሳሰብ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል።

ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የራሱ የኾነ ልዩ ባሕርያት አሉት።

· ሥልጣን ባለው አካል የሚደነገግ፣የሚተገበር፣ የሚሻሻል ነው።

ሲደነገግም ሲሻሻልም በግለሰቦች የግል ፍላጐት ወይም ፈቃድ የሚደነገግ ወይም የሚሻሻል አይደለም።

· ሃይማኖታዊ ይዘት አለው። ምክንያቱምዓላማው ሰውን ኹሉ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር ማፍለስ ስለኾነ ቄሣራዊ ይዘት የለውም። ቢኖርም እንኳን አንድ ክርስቲያን በዚኽምድር የሚኖረው ቆይታ ከሰማያዊ ሕይወቱ ጋር ሳይጣረስበት እንዴት መኖር እንዳለበት የሚያስረዳ ነው።

· የሰው ልጅ ከሚችለው በላይ ሸክምንአይጭንም፤ "ሸክሜ ቀሊል ነው" እንዲል /ማቴ.11፥29/።

· የሽላሚነትና የቀጪነት ሥልጣንአለው። ቄሣራዊ ሕግ የሽላሚነት ይዘት የለውም። በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ግን ለምሳሌ ተጋድሎአቸውን በድል ያጠናቀቁት ክርስቲያኖችቀን ተለይቶላቸው፣ ታቦት ተቀርጾላቸው በምእመናን ዘንድ ክብርን እስከ ማግኘት ይደርሳሉ። በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ የዘለዓለምአክሊል ዘውድ አለው።

· የአምልኮ ይዘት አለው። በውስጡጾም፣ ጸሎት፣ ምጽዋት እና የመሳሰሉትን ኹሉ ያካትታል።

· የመመዘን ጠባይ አለው። ለምሳሌየቃየን መሥዋዕት ያልሰመረችው መሥዋዕት ስላላቀረበ ሳይኾን በሕጉ መሠረት አሰስ ገሰስ ኾኖ ስለተገኘ ነው /ዘፍ.4/።

· በአንድ ጊዜ በአንድ ቦታ የተደነገገአይደለም።

· ሰዎችን ደስ ለማሰኘት አይወጣም፤የሚወጣው እግዚአብሔር ደስ ለማሰኘት ብቻ ነው። "ለዓለም ከሚመች ከንቱ ልፍለፋ ራቅ" እንዲል ለዓለም የሚመች ቀኖና አይወጣም።ቀኖና የሚወጣው የምእመናን

መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያድግና ምእመናን በሚኖሩበት ማኅበረ ሰብእ ውስጥ አርአያ እንዲኾኑ ነው።

· አንጻራዊ ጽድቅ ስለሌለ አንጻራዊቀኖናም የለም። ጥቁሩን ጥቁር ነጩንም ነጭ የሚል እንጂ የተድበሰበሰ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አታወጣም፤ እንዲኽ ካልኾነ የውጫሌሕግ ነው። በዓለማዊ ሕግ የወንጀሉ መጠን ይታያል። በቤተ ክርስቲያን ሕግ ግን ወንጀል ወንጀል ነው።

የቀኖናምንጮች

ዛሬ ላለው የቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና ምንጮቹ ልዩ ልዩ ቢኾኑም ጠቅለል ባለመልኩ ግን እንደሚከተለው ከፍለን ማየት እንችላለን።

ሀ)የሐዋርያት ሲኖዶስ

እነዚኽ መጻሕፍት በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. 81 ተብለው ከሚታወቁት መጻሕፍት የሚካተቱሲኾኑ ሐዋርያት በየጊዜው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እየተሰበሰቡ የደነገጓቸው እጅግ ጠቃሚ የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው። እነርሱም መጽሐፈዲድስቅልያና መጻሕፍተ ሲኖዶሳት (ትእዛዝ፣ ግፅው፣ አብጥሊስ፣ ሥርዓተ ጽዮን) ናቸው። ሲኖዶስ የተባለውና አራት ክፍል ያለው መጽሐፍበውስጡ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ስለ አገልጋዮች ማዕረጋት ቀኖና ይናገራል። መጽሐፈ ዲድስቅልያ ደግሞ ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርእና ሥርዓተ አምልኮን በዝርዝር ይናገራል።

እናስተውል! የጌታ ትእዛዛት በሙሉ ዶግማ ነው። ጾም፣ ጸሎት፣ጥምቀት፣ ቁርባን፣ ንስሐ፣ ከወንድም ጋር መታረቅ...ወዘተ ዶግማ ነው። ቀኖና የሚኾነው ዝርዝር አፈጻጸሙ ላይ ሲኾን ነው። ቀኖናከሐዋርያት የሚዠምረውም ለዚኹ ነው። በመኾኑም አንድ ሰው ተነሥቶ ጾም

አያስፈልግም ቢል የቀኖና ሳይኾን የዶግማ ጥሰት ነው።

ለ)ዓለም አቀፍ ጉባኤያት

ጉባኤያት ዓለማቀፋውያንጉባኤያት የሚባሉት ከኹሉም አብያተ ክርስቲያናት የመጡ ተወካዮች ሲኖሩበት ነው። የጉባኤው መነጋገሪያ አጀንዳም ዓለማቀፋዊ መኾንአለበት። የተወሰነው (የሚወሰነው) ውሳኔም በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተፈጻሚ መኾን አለበት። የነገሩ ጉዳይ ለአንዲትሀገር ብቻ የሚተው መኾን የለበትም። ለምሳሌ በ325 ዓ.ም. የተካሔደው የኒቅያ ጉባኤ ዓለማቀፋዊ አጀንዳን የያዘ (ዓለም ስለመዳኑናስላለመዳኑ)፣ ከኹሉም አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች የነበሩበት፣ ውሳኔውም በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተፈጻሚነት የነበረውነው።

በኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ዓለምአቀፍ ጉባኤያት ሦስት ሲኾኑ፤ ምሥራቃውያን 7፥ ካቶሊኮች ደግሞ 20 ይቀበላሉ።

ኦሬንታል አርቶዶክሶች የምንቀበላቸው ሦስቱም ጉባኤያት ጉባኤ ኒቅያ (በ325 ዓ.ም. የተካሔደ)፣ ጉባኤ ቁስጥንጥንያ (በ381 ዓ.ም. የተካሔደ) እና ጉባኤ ኤፌሶን (በ431 ዓ.ም. የተካሔደ) ናቸው። በእነዚኽዓለም አቀፍ ጉባኤያት ብዙ ቀኖናዎች ተደንግገዋል። ለምሳሌ በጉባኤ ኒቅያ ከተወሰኑት ቀኖናት የትንሣኤ በዓል እሑድ መከበር እንዳለበት፣ስለ አርዮስ ጉዳይ፣ ስለ መጻሕፍት ጉዳይ፣ ስለ አራቱ መንበረ ፓትሪያሪኮች ይገኙባቸዋል።

ሐ)ብሔራውያን ጉባኤያት

ከዓለማቀፋውያን ጉባኤያት በተጨማሪ በየአካባቢው ጉባኤያት ሊደረጉ ይችላሉ።ለምሳሌ በቅዱስ ያሬድ ዜማ ላይ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይዋ አይደለም። የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ አይደለም ብለን ግንበኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስር ኾነን ያሬዳዊ መዝሙር አያስፈልገንም ወይም በኦርጋንና በፒያኖ እንዘምር ማለትአንችልም። እነርሱ በያሬዳዊ መዝሙር ስላልዘመሩ ብለንም ሃይማኖታዊ (የዶግማ) ወይም የቀኖና ችግር አለባቸው አንልም፤ ውሳኔውበብሔራዊ ጉባኤ የተወሰነ ነውና።

ከብሔራውያን ጉባኤያት በተጨማሪ ሀገረ ስብከታዊ ጉባኤም ሊደረግ ይችላል።አጥቢያዊ ጉባኤም ሊኖር ይችላል። ነገር ግን በአንድ ሀገረ ስብከት የተወሰነው ውሳኔ በሌላ ሀገረ ስብከት ተፈጻሚ ላይኾን ይችላል።በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሠራ ቀኖናም በሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይሠራ ይችላል። በኢትዮጵያ ውስጥ በአንዳንድ ገዳማትላይ ሴቶች አይገቡም የሚባለው የዚያ ገዳም ብቻ ቀኖና ስለሚኾን ነው።

መ)የቅዱሳን አበው ቀኖናት

እነዚኽ ቀኖናት ምንም እንኳን በግለሰብ ደረጃ የተወሰኑ ቢኾኑም ቤተ ክርስቲያንየእኔ ብላ የተቀበለቻቸው ቀኖናት ናቸው። ለምሳሌ ሥርዓተ ምንኵስና የነ አባ እንጦንስ ወይም የእነ አባ ጳኵሚስ ሃይማኖት አይደለም፤የእነዚኽ ቅዱሳን አባቶች የትሩፋት ሥራ እንጂ። አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስለ ቅዱስ ቁርባን የተናገረው ሥርዓት የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ.ሥርዓት ኾኖ የቀረውም ከዚኽ አንጻር ነው። የቅዱሳን ገድላትና ድርሳናትም እንደምንጭነት ይጠቀሳሉ።

የቀኖናቤተ ክርስቲያን ይዘት

ቤተ ክርስቲያናዊ ቀኖና በውስጡ በጣም ብዙ ነገሮችንያካተተ ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና፣ የሥርዓተ አምልኮ ቀኖና፣ የአጽዋማት ቀኖና፣ የበዓላት ቀኖና፣ የቅዱሳን ቀኖና፣ የቅዱሳትሥዕላት ቀኖና፣ የአለባበስ ቀኖና ተጠቃሾች ናቸው። እስኪ ጥቂቶቹን ብቻ እንደማሳያ በአጭር በአጭሩ ለማየት እንሞክር፡-

1. የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና

የቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና ስንል የመጻሕፍቱ እውነተኛነትን፣ ቅዱስነትንና አምላካዊነትንየተመለከተ ማለታችን ነው። እነዚኽን ቅዱሳት መጻሕፍት ሰፍረውና ቈጥረው የሰጡንም ሉተራውያን ወይም ካቶሊካውያን ሳይኾኑ ኦርቶዶክሳውያንአባቶቻችን ናቸው። በተለይም እነ ቅዱስ ሄሬኔዎስ፣ ቅዱስ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ፣ ቅዱስ አትናቴዎስ በዚኽ ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚኽ ቅዱሳን አባቶች የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ለመቀበል ያስቀመጧቸው መስፈርቶችነበሩ። ከእነዚኽም መካከል፡-

ü ወደ ግሪክኛ የተተረጐመ። አባቶች ይኽን ያሉበት ዋናው ምክንያት አይሁዳውያኑየጌታችንን የባሕርይ አምላክነት ካለመቀበላቸው የተነሣ ብሉይ ኪዳንን ቈነጻጽለዉት ስለነበር ነው። ስለዚኽ ከዚኽ ከተቈነጻጸለውመጽሐፍ ሊመጣ ከሚችለው ግድፈት ለመዳን አይሁዳውያኑ ይኽን እንደሚያደርጉ አስቀድሞ የሚያውቅ እግዚአብሔር በ285 ቅ.ል.ክ. ላይወደ ግሪክኛ የተተረጐመው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ መቀበል ግድ ኾኖባቸዋል።

ü የዕብራውያን ባሕል ያለበት። አባቶችመጽሐፉ የዕብራውያን ባሕል ያለበት መኾን አለበት ያሉበት ምክንያት እግዚአብሔር አስቀድሞ

ለዕብራውያኑ በባሕላቸው ስለነገራቸው ነው።መጽሐፉ ዕብራዊ ባሕል ከሌለበት ተቀባይነት አያገኝም።

Ü የአብርሃም እምነት ያለበት። የአብርሃም እምነት መኾን አለበት ሲሉም ከአንድ አምላክ በቀር ወደባዕድ አምልኮ የሚመሩትን መጻሕፍት ለመለየት ነው።

የሰባ ሊቃናት ትርጒም የምንለውም ይኽን ቀኖና ተከትሎ የተሠራ ትርጒም ነው።በ 2000 ዓ.ም. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ. ያሳተመችው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሙ አብዛኛው ከዚኹ ትርጒም የተወሰደ ነው።

እናስተውል! በአንዳንድ የአማርኛ ትርጒሞች ላይ(ለምሳሌ በ 1980 ዓ.ም. እትም ላይ) በስሕተት ተጽፎ የምናገኘው ቢኾንም በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ዴትሮካኖኒካልየሚባሉ መጻሕፍት የሉም። ዴትሮካኖኒካል የሚሉት ካቶሊኮች ናቸው። ይኸውም ተጨማሪ መጻሕፍት ለማለትነው። ነገር ግን እነዚኽ መጻሕፍት ከመዠመሪያውኑ የነበሩ እንጂ በኋላ የተጨመሩ አይደሉም። ለዚኽ ማረጋገጫውም በ 1948 ዓ.ም.ላይ በሙት ባሕር ላይ በተገኙት ጥቅሎች እነዚኽ ተጨማሪ ናቸው ተብለው የታሰቡት መጻሕፍት በዕብራይስጥ ተጽፈው መገኘታቸው ነው።ስለዚኽ አይሁዳውያኑ በ 280 ዓ.ም. ላይ ታናክ የሚሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቀኖና ሲሠሩ የሰባ ሊቃናቱን ትርጒም የክርስቲያኖችመጽሐፍ ነው ብለው ስለቈነጻጸሉትና ስለቀነሷቸው እንደተጨማሪ መጻሕፍት ማየት (ዴትሮካኖኒካል ናቸው ማለት) በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያንአስተምህሮ ያልነበረ ነው።

አኹንም እናስተውል! እነዚኽን መጻሕፍት

እንደፕሮቴስታንቱ ዓለምም አፖክሪፋ አንላቸውም። አፖክሪፋ ማለት በግሪክኛ የተሰወረ፣ ያልተገለጠ፣ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠ ለማለትነው። ፕሮቴስታንቱ ዓለም ይኽን እንዲል ያደረገው ዋናው ምክንያት ከላይ እንደገለጽነው አንደኛ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍቱንተጨማሪ ናቸው ስላለችና እነርሱም ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሲወጡ ተጨማሪ የሚለውን ቃል ብቻ ይዘው ተጨማሪ አያስፈልገንም በማለት፤ኹለተኛ አይሁዳውያኑ የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት ላለመቀበልና ለክርስቲያኖች በነበራቸው የመረረ ጥላቻ በተንኰል የቈነጻጸሉትንመጽሐፍ ያለምንም ጥያቄ ስለተቀበሉት ነው። ስለዚኽ ራሳችንንና ወንድማችንን ከእንደዚኽ ዓይነት ኦርቶዶክሳዊ ያልኾነ ትምህርት ልንጠነቀቅይገባል። አብዛኞቹ የእንግሊዘኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጕሞች የተተረጐሙት ከዚኹ አይሁድ ከቈነጻጸሉት ቀኖና የተወሰደ መኾኑንም ማስታወሱተገቢ ነው። ደኅና ነው ተብሎ የሚታሰበው “Revised Standard Version” የሚባለው ነው። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የሐዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ለመለየት የተጠቀሙበትመስፈርትም አለ። እርሱም፦

Ü ሐዋርያት ወይም የሐዋርያት ደቀ መዛሙርት የጻፉት መኾን አለበት፤

Ü ከ99 ዓ.ም. በፊት መጻፍ አለበት። ይኽንያሉበት ዋና ምክንያትም ከ105 ዓ.ም. በኋላ የግኖስቲኮች የክሕደት መጻሕፍት በስርጭት ላይ ስለነበሩ ነው።

Ü የክርስቶስና የሐዋርያት ትምህርት የሚገልጽ መኾን አለበት።

አንድ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ቅዱሳት መጻሕፍትን (አሥራውም ይኹኑ አዋልድ) ሲለይከምንም በላይ ማየት ያለበት ቁጥሩን (81፣ 66፣ 73፣

76 የሚለውን) ሳይኾን ኦርቶዶክሳዊ ይዘታቸውን ነው። አንድ መጽሐፍኦርቶዶክሳዊ ይዘት እንዳለው የሚታወቀውም፦

· ነገረእግዚአብሔርን የሚያስክድ ካልኾነ። ለምሳሌ የጀሆቫ ዊትነስ፣ የሞርሞን አማኞች ያዘጋጁት “መጽሐፍቅዱስ” ፍጹም ክሕደት ነው።

· የሚፃርትይዘት ከሌለው። ምንም እንኳን ተጨማሪ ሥራ የሚጠይቅ ቢኾንም የዚኽ ጽሑፍ አዘጋጅ እስከ አኹን ድረስ ባለውመረጃ መሠረት በሐዲስ ኪዳን ኅቡእ ስም የለም። ምንም እንኳን በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችን ድርሳናት ላይ እንዲኽ ዓይነት ጽሑፍብናገኝም ወደ ኋላ ስንሔድና የዚያ ድርሳን ጥንታዊውን የብራና ጽሑፍ ስንመለከት ግን ጸ፣ጸ፣ጸ፣ጸ፣ጸ፣ጸ፣ ጨ፣ ጨ፣ ጨ፣ ጨ፣ ገ፣ገ፣ ገ፣ ገ፣ ገ... የሚል ኅቡእ ስም የለውም። እነዚኽ ኅቡእ ስሞች በኋላ ላይ በስርዋፅ የገቡ ናቸው። አኹን አኹን የሚታተመውንድርሳነ ሚካኤልን እንደ አንድ ማሳያ ብንወስደው ከ 15 ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በነበረው የድርሳነ ሚካኤል የብራና ጽሑፍ ላይ እንዲኽዓይነት ኅቡእ ስም የለውም። ዘወትር ለጸሎት በምንጠቀምበት በወንጌል፣ በመዝሙረ ዳዊት፣ ወይም በውዳሴ ማርያም ኅቡእ ስም የለም።ኅቡእ ስም ተብሎ በብዛት የምናገኘው በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ በግለሰቦች በሚታተሙት መጻሕፍት ላይ ነው /የቃልመረጃ ከመምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል፣ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የቀኖና ቤተ ክርስቲያን መምህር/። በመኾኑምበቤተ ክርስቲያናችን በአዋልድ መጻሕፍት ቀኖና ዙርያ ብዙ የሚቀር ሥራ እንዳለ ያመለክታል። የሚመለከታቸው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንምየድርሻቸውን እንደሚወጡ እምነታችን ነው።

· እምነታችንንከእግዚአብሔር አውጥቶ ለሌላ አካል አሳልፎ የሚሰጠን ካልኾነ። ለምሳሌ ይኽን ቃል ደጋግመኽ በለው ካለ፤ የፈጣሪንሥራ በሌላ የሚቀይር ከኾነ፤ ከዚኽ ከዚኽ የሚያድኑ ጸሎቶች የሚል ከኾነ፤ በትራስኽ ላይ ብትንተራሰው ካለ፤ ይኽን ክታብ በአንገትኽላይ ብታንጠለጥለው የሚል ዓይነት ከኾነ ያለ ምንም ቅድመ ኹኔታ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት እንዳልኾኑ ዐውቀን ልንጥላቸው ይገባል።

2. የቅዱሳን ቀኖና

በቀኖና ወይም በሥርዓት ደረጃ ቅዱሳንን ማክበር የተዠመረው ከኹለተኛው መቶክፍለ ዘመን አንሥቶ ነው። ነገር ግን ይኽን ያደረገው ቅዱስ ሲኖዶስ ሳይኾን ሕዝቡ ወይም ምእመኑ ራሱ ነው። በዚኽም ቀድመውይታሰቡና ይከበሩ የነበሩት ቅዱሳን ሰማዕታት ናቸው። ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዠምሮ ግን አንዳንድ ሰዎች በራሳቸው እይታ ቅዱስእንደኾነ የሚያስቡትን ኹሉ ቅዱስ ለማስባል ስለተነሣሡ ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ ደረጃ ቀኖና ቅዱሳን ማውጣት ዠመረች። ቤተ ክርስቲያንቀኖና ቅዱሳን ማውጣት ዠመረች ማለት ግን ለሰዎቹ ቅድስናን ሰጠች ማለት ሳይኾን ለቅድስናቸው ዕውቅናን ሰጠች ለማለት ነው። ይኸውምከትሩፋታቸው ብዙ እንድንማር፣ በቃል ኪዳናቸው እንድንጠቀም፣ አሰረ ፍኖታቸውን እንድንከተል፣ አማላጅነታቸውን እንድንጠይቅ ነው።

አንድን ቅዱስ ቅዱስ ለማለት መስፈርቶች አሉት። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያኽል፡-

· ከምንም በፊት ክርስቲያን መኾን አለበት። አምኖ የተጠመቀ፣ ቅዱሳት ምሥጢራትንሲፈጽም የኖረና ከእኩያት ጋር የተጋደለ መኾን

አለበት። አለበለዚያ ክርስቲያን ሳይኾኑ (ካቶሊክም ፕሮቴስታንትም ጭምር) የፈለገያኽል በጐ ምግባር ቢኖራቸውም ቅዱሳን አይባሉም።

· በክርስቲያናዊ ምግባራቸው የታወቁ። ሃይማኖት ያለ ምግባር የሞተ ነውና።እንዲኽ ሲባልም ፈጽመው ኃጢአት ያልሠሩ ለማለት አይደለም፤ እንዲኽ ያለ ዕሩቅ ብእሲ ከእመቤታችን በቀር ማንም አይገኝምና።

· ገቢረ ተአምራትን የፈጸሙ። እንዲኽ ሲባልም ተአምራትን ማድረግ ብቻውንመስፈርት ሊኾን እንደማይገባ ሊታወቅ ይገባል /ማቴ.7፡21/።

· ቅዱሳኑ ካረፉ በኋላ ዓጽማቸው ሕሙማንን ከፈወሰ፤ ባረፉበት ቦታ ጠበል ከፈለቀ።

· ለየት ያለ አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን ካበረከቱ። ለምሳሌ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ.እነ ቅዱስ ላሊበላ፣ እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ እነ አቡነ ጴጥሮስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያደረጉትን አስተዋጽኦ ማስታወሱበቂ ሊኾን ይችላል።

እንዲኽ በቀኖናው መሠረት ቅዱስ የተባለው ታላቅሰው ቅድስና ሲሰጠው የሚከተሉት ነገሮች ይፈጸሙለታል፡-

V በስሙቤተ ክርስቲያን ይታነጽለታል፤

V ገድልይጻፍለታል፤

V በዓልይደረግለታል፤

V ቅድስናውንአጒልቶ የሚያሳይ ሥዕል ይሣልለታል፤

V ዐፅሙበክብር እንዲያርፍና ምእመናን እንዲያከብሩት ይደረጋል፤

V ምእመናንበስሙ ሊሰየሙና ውሉደ እግዚአብሔር ሊባሉ ይችላሉ /በዓላትምን? ለምን? እንዴት?፣ በዲ/ን ብርሃኑ አድማስ፣ 2005

ዓ.ም.፣ ገጽ 144-145/።

3. የሥርዓተ አምልኮ ቀኖና

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንፈጽመው ማንኛውም ዓይነት መንፈሳዊ ድርጊት የአምልኮባሕርይ አለው። ስናምን፣ ስንሰጥ፣ ስንቀበል ኹሉ አምልኮ ነው። ማንኛውንም ዓይነት ምሥጢር ስንፈጽም የእግዚአብሔር መኾናችንንነው የምንገልጠው።

ያለ ሃይማኖት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን መቀበል አይቻልም። የእግዚአብሔር ሀብትከእግዚአብሔር ጋር በመኾን እንጂ እንደ ሲሞን መሠሪ የምንገዛው አይደለምና።

ሃይማኖት መታዘዝንም ይጨምራልና እንደ ቀኖና ዲያቆኑን፣ ቄሱን ወይም ጳጳሱንማክበር ይጠበቅብናል። በጉድለት፣ በትዕቢት፣ በጭቅጭቅ የምንቀበል ከኾነ አለመታዘዝ ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ደናግላን ሳይኾኑተክሊል ካልተደረገልን ብለው ይጨቃጨቃሉ። በዚኽም ምሥጢረ ተክሊልን ሲፈጽሙ አምልኮተ እግዚአብሔር እየፈጸሙ እንደኾኑ ይረሳሉ።ከሥርዓተ አምልኮው ይልቅ በቤታቸው ስለሚሰቅሉት ፎቶ ይጨነቃሉ። ስለዚኽ ቀኖናና አምልኮ በእጅጉ የተቈራኙ መኾናቸውን ዐውቀን በቤተክርስቲያን ውስጥ በምንፈጽማቸው መንፈሳዊ ድርጊቶች ላይ ልንጠነቀቅ ይገባናል።

4. ሥርዓተ ሲመትን የሚመለከት ቀኖና

በጥምቀት የተወለደ ኹሉ አገልጋይ ነው፤ “ያገለግሉኝዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ” እንዲል /ዘጸ.8፥1/። ይኸውም አሥራቱን ቀዳምያቱን የሚያወጣ፣ የሚታዘዝ ሕዝብ ይኾነኝ ዘንድ ማለት ነው።ከእነዚኽ ከተጠመቁት ተመርጠው የሚያገለግሉት ደግሞ ስዩማነ ካህናት (የአገልጋዮች መሪዎች)

ይባላሉ። እነዚኽን ስዩማነ ካህናትለመሾምም የራሱ የኾነ መስፈርት አለው። ይኽን መስፈርት ሳያሟላ ማንም ራሱን ሊሾም አይችልም። ከ 12 ቱ ሐዋርያት አንዱ ይሁዳሲጐድል ሐዋርያት በይሁዳ ፈንታ ሌላ አንድን ሐዋርያ ለመሾም ሲጾሙ፣ ሲጸልዩ፣ ዕጣ ሲጥሉ፣ እጅግ ተጨንቀው ይኽን ኹሉ ሲያደርጉማየታችን ኹሉም ሰው ሐዋርያ እንዳልኾነ የሚያስረዳ ነው። በሌላ አገላለጽ አንድን ክርስቲያን ስዩመ ካህን ለማድረግ የራሱ መስፈርትእንዳለው የሚያስገነዝብ ነው።

በአጠቃላይ ቀኖና እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም፡-

1. የፍላጐት ልዩነት በሰዎች መካከል አይቀሬ ነው። እነዚኽን ሰዎች ወደ ስምምነት ለማምጣትደግሞ የግድ ሕግ ያስፈልጋል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ አለመስማማቶችን የሚፈታ ነው።

2. በሰውነታችን ውስጥ ያሉት ብልቶች የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። ብዙዎች ቢኾኑም አንድሰውነት ናቸው። ብዙዎች ኾነው ሳለ የአንድ ሰውነት አባል ኾነው መቀጠል የሚችሉት ግን እጅ የእግርን፣ ዓይን የዦሮን ሥራ ልሥራእስካላለች ድረስ ብቻ ነው። እንዲኽ ሕገ ተፈጥሮን ጥሶ መዘበራረቅ ካለ ሰውነት እንደ ሰውነት መቀጠል አይችልም። ልክ እንደዚኹእኛ ክርስቲያኖችም ብዙዎች ብንኾንም የአንድ ክርስቶስ ብልቶች ነን። የአንድ ክርስቶስ ብልቶች ኾነን የምንቀጥለው ግን ካህኑ የክህነቱንምእመናንም የምእመናንን ሥራ የሠራን እንደኾነ ብቻ ነው። አንዱ ምእመን ተነሥቶ የካህኑን ሥራ ልሥራ ቢል የቤተ ክርስቲያን አንድነትሊጠበቅ አይችልም። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ይኽ አንድነት እንዲኖር ይረዳል።

3. ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነታችን መብታችንና ግዴታችንን ለይቶየሚነግረን ነው። ለምሳሌ አንድ ምእመን ዐሥራት በኲራት የማውጣት ግዴታ አለበት። ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መገዛት አለበት። ይኽን ሳያደርግ ቀርቶ ከቤተ ክርስቲያን መጥቶ ምሥጢራትን ልፈጽም ቢል ተቀባይነት የለውም። የቤተ ክርስቲያን ሕግስ ይቅርና የትራፊክሕግም ጥቅሙ ብዙ ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

ወዲ ዓባይ ካሕሳ ፃዕዱ added 2 new photos .

8/ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የምትገለገልባቸው የዶግማ፤የቀኖና እና የታቦት ምንነት በመጽሃፍ ቅዱስ ኣስደግፈህ ንገረኝ ላልከው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ወንድሜ Olyad Gamachis መልስ፦

እኔም ኣንተን በመጠየቅ እግዚኣብሄር በፈቀደልኝ መጠን ወደ መልስ እሄዳለሁ።

ጥያቄየ፦

1)የእግዚኣብሄር ስራዎች በግዜ ለተወሰኑ ኣገልግሎት የሚሰጡ ህጎችና ስርኣቶች ናቸው?

2)እግዚኣብሄር ጣዖትን ይሰራል?

3)ኣሁን ጴንጤዎች ለተከታዮቻችሁ ቁርባን ማቁረብ ጀምራችኋል። ይህም እናንተ የክርስቶስ ስጋ ወደሙ ለሰዎቻቹህ እያበላችሁና እያጠጣችኋቸው

ነው። ታድያ ኣሁን ከየት የተገኘ የክርስቶስ ስጋና ደም ነው እናንተ እያዘጋጃችሁት ያለው ቁርባን?

4)እግዚኣብሄርም ስትጸልዩ<<ኣባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግስትህም ትምጣ ....>>ኣለ። መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐ 15-3 ፤ማቴ 6:7፤ጌታም ጸሎትን ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምራቸው "በሰማይ የምትኖር ሆይ " ብለው እንዲጀምሩ መከራቸው።ይህም በራሱ ወደሰማይ ቀና ብሎ ኣለው።

ታድያ እናንተ ለምን ኣባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ብላችሁ ኣትጸልዩም?

ለምንስ ወደቁልቁል ኣቀርቅራቹ ኣይናችሁን በመጨፈን የማይሰማ ጸሎት ትጸልያላቹ?

5)ማቴዎስ 5፤18 ን ስናነብ 'እኔ ህግንና ነብያትን ልሽር አልመጣሁም' ሲል ምን ማለቱ ነው?

6)ጌታችን 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሟል፤ታድያ እናንተ ይህን የሱ ቃል ለምን ኣትፈጽሙም?

ወደ ጥያቄህ መልስ እንሂድ፦

ትምህርት ሃይማኖት (የሃይማኖት ትምህርት) በሁለት ይከፈላል። ይኸውም፦

1 ኛ፡- ዶግማ 2 ኛ፡- ቀኖና በሚል ነው።

ዶግማ፡- ቃሉ የግሪክ ሲሆን ፍችውም እምነት ማለት ነው።

ቀኖና፡- ደግሞ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ሥርዓት ማለት ነው።

ከእነዚህ ከሁለቱ ዶግማ ወይም እምነት አይጨመርበትም፤ አይቀነስበትም፤ አይሻሻልም፤ ችግርና ፈተናም ቢመጣ እስከ ሞት ድረስ አጥብቀን

የምንይዘው ነው። ለምሳሌ ያህል ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ፤ ቢመረምር እንጂ የማይመረመር ሁሉን ቻይ አምላክ፤ የሚሳነው ነገር የሌለ ፈጣሪ፤ የሰማይና የምድር ባለቤት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር (ፈጣሪ) የአካል ሦስትነት አለው። በመለኮት፣ በመፍጠር፣ በሥልጣን፣ በአገዛዝ፣ በፈቃድ ግን አንድ ነው። በሦስትነቱ አብ፤ ወልድ፤ መንፈስ ቅዱስ ሲባል በአንድነቱ አንድ መለኮት አንድ እግዚአብሔር ይባላል። በአዳም ምክንያት ከመጣው የዘለዓለም ሞትና ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ የወጣነው ከሦስቱ አካላት በአንደኛው አካል ማለትም በወልድ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ዶግማ ወይም እምነት ይባላል።

ቀኖና ግን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ያደጉ ክርስቲያኖች የሚመሩበት ሥርዓት ስለሆነ፤ በሃይማኖት አባቶች ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት እንደጊዜው ሁኔታ የሚሻሻል በመሆኑ የሚጨመርበት፤ የሚቀነስለት ነው። ለምሳሌ ያህል እኛ ኦርቶዶክሳውያን የምንጠመቀው ሴት በሰማንያ ወንድ በአርባ ቀናችን ነው። የተወለዱ ሕጻናት ሴቷ ሰማንያ ወንዱም አርባ ቀን ሳይሞላቸው ቢታመሙና በሽታው አስጊ ከሆነ በ 10፣ በ 20፣ በ 30…ቀናቸው መጠመቅ ይችላሉ ቀኖና ነውና።

በቤተ ክርስቲያናችን የቀዳስያን ብዛት መነሻው አምስት ነው። ምናልባት ከአምስቱ አንዱ፤ ሁለቱ፤ ሦስቱ ቢታጡና ሌላም ተፈልጎ እስከ መጨረሻ የማይገኝ ከሆነ ከአቅም በላይም የሆነ ችግር ከገጠመ ሁለቱ ወይም አንዱ ብቻ ቀድሰው ማቁረብ ይችላሉ። ቀኖና ነውና። በቤተ ክርስቲያናችን ታቦት ሲከብር ቤተ ክርስቲያኑን የሚዞረው ሦስት ጊዜ ነው ችግር ካለ አንድ ጊዜ

ብቻ ዑደት ተፈጽሞ ሊገባ ይችላል። ቀኖና ነውና፤ ስለቀኖና (ስለሥርዐት) ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ እንዲህ ሲል ጽፏል።

1. <<ነገር ግን ሁሉን በአግባብና በሥርዐት አድርጉ።>> 1ኛ ቆሮ. 14፥40።

2. <<ወንድሞች ሆይ በሠራንላቸው ሥርዐት ሳይሆን በተንኮል ከሚሄዱት ወንድሞች ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን። እኛን ልትመስሉ እንደሚገባችሁ እኛም በእናንተ መካከል ያለ ሥራ እንዳልኖርን ራሳችሁ ታውቃላችሁ>> 2ኛተሰ. 3፥6-7

ቀኖና (ሥርዐት) የሚወሰነው በሃይማኖት አባቶች እንደሆነና ወንጌልን የሚስተምር ሰው ለሚያስተምራቸው ክርስቲያኖች በሃይማኖት አባቶች የተወሰነ ቀኖና ማስተማርና መስጠት እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያስረዳል።

በየከተማውም ሲሄዱ፥ ሐዋርያትና ቀሳውስት በኢየሩሳሌም ያዘዙትን /የወሰኑትን/ ሥርዐት አስተማሯቸው። አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ጸኑ ዕለት ዕለትም ቁጥራቸው ይበዛ ነበር።>> ይላል የሐዋ. 16፥4-5።

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ ደርቤንና ልስጥራን በተባሉ ቦታዎች ለነበሩ ክርስቲያኖች ወንጌልን ከሰበከ በኋላ ሐዋርያት የወሰኑትን ቀኖና (ሥርዐት) እነደሰጣቸው እንረዳለን።

ስለዚህ ቀኖና ወይም ሥርዐት ቤተክርስቲያንን ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም። በመሆኑም ዶግማንና ቀኖናን ወይም እምነትንና ሥርዓትን ጎን ለጎን ይዞ መጓዝ ሐዋርያትን መከተል እንጂ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሁድን መከተል አይደለም።

እንግዲህ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን የሚቃወሙ ሰዎች ሁሉ፤ የሚቃወሙት በቀኖና (በሥርዐት) የሚመሩትን ክርስቲያኖች ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል የሆነ መጽሐፍ ቅዱስን ነው።

አሁን እንግዲህ የዶግማንና የቀኖናን ልዩነት ከተረዳን በቀጥታ ወደ ታቦቱ ጥያቄህ እንሄዳለን።

ጥያቄ፡-1 ዛሬ በእኛ ቤተክርስቲያን ያለው ታቦት ነው? ወይስ ጽላት? ምክንያቱም በታቦትና በጽላት መካከል ልዩነት አለና።

መልስ፡- ታቦት የጽላት ማደሪያ ነው። ዘጸ 40፥20። ጽላት ደግሞ ቅዱስ ቃሉ የተጻፈበት ሰሌዳ ማለት ነው። ዘጸ 34፥27-28።

የታቦትን ወይም መጽሐፍ ቅዱስ በአብዛኛው እንደሚጠራው "የኪዳን ታቦት" ወይም "የምስክር ታቦት"ን ምንነት በሚገባ ለመረዳት ደግሞ ታቦቱ የተሰጠበትን የብሉዩን ቃል ኪዳን መረዳት ያስፈልጋል። ታቦት ወይም "የቃል ኪዳን ታቦት" እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በሙሴ በኩል የገባው የቃል ኪዳኑ ምልክትና ምስክር ነው። ስለዚህ የኪዳኑን ታቦት ምንነት ለመረዳት ኪዳኑን ወይም ቃል ኪዳኑን ራሱን መረዳት ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር የቃል ኪዳን አምላክ ነው። በተለያዩ ጊዜያት እግዚአብሔር ከግለሰቦችና ከእስራኤል ሕዝብም ጋር ቃል ኪዳን ገብቶአል። ከግለሰቦች ጋር ከገባቸው ቃል ኪዳኖች ውስጥ ከኖህ፤ ከአብርሃምና ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ደግሞ ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት ነጻ ካወጣቸው በኋላ በምድረበዳ በሲና ተራራ የገባው ቃል ኪዳን ማለትም ብሉይ ኪዳን ወይም የቀድሞው ኪዳን የሚጠቀስ ነው።

ቃል ኪዳን ማለት በሁለት ሰዎች ወይም በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የሚገባ የስምምነት ውል ነው። ስለዚህ የብሉዩንም ይሁን የአዲሱን ቃል ኪዳን ለመረዳት የስምምነቱ ውል ይዘት ምን እንደሆነና ቃል ኪዳን ተጋቢዎቹስ እነማን እንደሆኑ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ግልጽ ከሆነልን በብሉይና በአዲስ ኪዳን ልዩነት ዙሪያ የምንጠይቃቸው ብዙ ጥያቄዎቻችን ይመለሱልናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘጸዐት ከምዕራፍ 19-24 ላይ ስናነብ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር እንዴት ብሉይ ኪዳንን እንደሰጣቸው ወይም ከእነርሱ ጋር እንዴት ቃል ኪዳን እንዳደረገ እንመለከታለን።

በመጀመሪያ በምዕራፍ 19 ላይ እግዚአብሔር ራሱ በሲና ተራራ ላይ እንደወረደና በቀጥታ እንደተናገራቸው እናያለን።

ዘጸአት 19፤1 በሦስተኛውም ወር የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ በኋላ በዚያ ቀን ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ።

ዘጸአት 19፤2 ከራፊድም ተነሥተው ወደ ሲና ምድረ በዳ መጡ፥ በምድረ በዳም ሰፈሩ በዚያም እስራኤል በተራራው ፊት ሰፈረ።

ዘጸአት 19፤3 ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ወጣ እግዚአብሔርም በተራራው ጠርቶ አለው። ለያዕቆብ ቤት እንዲህ በል፥ ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ንገር።

ዘጸአት 19፤4 በግብፃውያን ያደረግሁትን፥ በንስርም ክንፍ እንደተሸከምኋችሁ፥ ወደ እኔም እንዳመጣኋችሁ አይታችኋል።

ዘጸአት 19፤5 አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥

ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ

ዘጸአት 19፤6 እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ። ለእስራኤል ልጆች የምትነግራቸው ቃል ይህ ነው።

ዘጸአት 19፤16 እንዲህም ሆነ በሦስተኛው ቀን በማለዳ ጊዜ ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምጽ በተራራው ላይ ሆነ በሰፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተንቀጠቀጡ።

ዘጸአት 19፤17 ሙሴም ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለማገናኘት ከሰፈር አወጣቸው ከተራራውም እግርጌ ቆሙ።

ዘጸአት 19፤18 እግዚአብሔርም በእሳት ስለ ወረደበት የሲና ተራራ ሁሉ ይጤስ ነበር ከእርሱም እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር፥ ተራራውም ሁሉ እጅግ ይናወጥ ነበር።

ዘጸአት 19፤19 የቀንደ መለከቱም ድምፅ እጅግ በበረታና በጸና ጊዜ ሙሴ ተናገረ እግዚአብሔርም በድምፅ መለሰለት።

እግዚአብሔር እንደዚህ በነጎድጓድና በመብረቅ ድምጽ በምድርም መናወጥ በሲና ተራራ ለእስራኤል ሕዝብ ከተገለጠ በኋላ ዘጸአት በምዕራፍ 20 አሥርቱን ትዕዛዛት ለሕዝቡ ይሰጣቸዋል።(ጽላቱ ላይ ያሉት አሥርቱን ትዕዛዛት)

እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የገባው ይህ ቃል ኪዳን ያካተተው አሥርቱን ትዕዛዛት ብቻ አይደለም። አሥርቱን ትዕዛዛት ጨምሮ ከዘጸአት ምዕራፍ 20 እስከ ምዕራፍ 23 ያሉትን የተለያዩ ሕጎችን ሁሉ ያካተተ ነው። ከምዕራፍ 20 እስከ ምዕራፍ 23 ብዙ ሕግጋትን ሕዝቡ እንዲጠብቁ እግዚአብሔር ከነገራቸው በኋላ ሕዝብም እነዚህን ሕግጋት

እንደሚጠብቁ ቃል ገብተው ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋሉ።በምን ? በታቦትና በጸላት በተጻፉ አሥርቱን ትዕዛዛት።

ኦሪት ዘጸአት 24፤3 ሙሴም መጣ፤ ለሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃሎች ሁሉ ሥርዓቱንም ሁሉ ነገረ፤ ሕዝቡም ሁሉ በአንድ ድምፅ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃሎች ሁሉ እናደርጋለን ብለው መለሱ።

ዘጸአት 24፤4 ሙሴም የእግዚአብሔርን ቃሎች ጻፈ።(ልብ በሉ ፤ህዝቡ በጣዖት ሲያመልኩ ባየ ጊዜ ሙሴ እግዚኣብሄር የሰጠውን ጽላት ጥጃው ላይ ስለወረወረውና ለ 2 ስለተሰበረበት እንደገና 10 ቱ ትእዛዛት በሌላ የከበረ ዲንጋይ ላይ ጻፋቸው።ስለዚህ ሌላ ኣዲስ ታቦት ሰራ ማለት ነው።) ማለዳም ተነሣ፥ ከተራራውም በታች መሠዊያን፥ አሥራ ሁለትም ሐውልቶች ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ሠራ።

ዘጸአት 24፤5 የሚቃጠል መሥዋዕት እንዲያቀርቡ፥ ለእግዚአብሔርም ስለ ደኅንነት መሥዋዕት በሬዎችን እንዲሠዉ የእስራኤልን ልጆች ጐበዛዝት ሰደደ።

ዘጸአት 24፤6 ሙሴም የደሙን እኩሌታ ወስዶ በቆሬ ውስጥ አደረገው የደሙንም እኩሌታ በመሠዊያው ረጨው።

ዘጸአት 24፤7 የቃል ኪዳኑንም መጽሐፍ ወስዶ ለሕዝቡ አነበበላቸው እርሱም፦ እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን እንታዘዛለንም አሉ።

ዘጸአት 24፤8 ሙሴም ደሙን ውስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨው። በዚህ ቃል ሁሉ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያደረገው የቃል ኪዳኑ ደም እነሆ አለ።

ስለዚህ እነዚህ ማቴዎስ 5፤18 ን ስናነብ 'እኔ ህግንና ነብያትን ልሽር አልመጣሁም' እንዳለ ፤ሁለት ነገሮች ዛሬም በሐዲስ ኪዳን አሉ። ሆኖም

ግን አሠራሩ ሙሉ በሙሉ በዘጸ 25፥10-18 ያለውን የሙሴን ሕግ የተከተለ አይደለም።

ምክንያቱም፦

1ኛ፡- ታቦት እንደሙሴ ሕግ የሚዘጋጀው ከግራር እንጨት ሆኖ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፤ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ቁመቱም አንድ ተኩል ይሁን ይልና በውስጥና በውጭም በጥሩ ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ አክሊል አድርግለት ይላል። ደግሞም ታቦቱን የሚሸከሙት ከወርቅ በተሠሩ መሎጊያዎች አራት ሰዎች እንደሆኑ እንረዳለን። በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን የታቦት አሠራር እጅግ ከባድ በመሆኑ በሁሉም ዘንድ አይቻልም ነበር። ምናልባት አንዳንድ የቤተክርስቲያን ፍቅር የነበራቸው ነገሥታትና ዛሬም ፍቅረ ቤተክርስቲያን ያላቸው አንዳንድ ምዕመናን ይችሉት እንደሆነ ነው እንጂ።

2ኛ፡- ጽላት፤ ጽላትም እንደሙሴ ሕግ ከሆነ መዘጋጀትና መጠረብ ያለበት ከከበረ ድንጋይ ነው። በአንድ ታቦት ውስጥም መቀመጥ ያለባቸው ሁለት ጽላቶች ናቸው። ዘጻ 34፥1። በአጠቃላይ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ሕግና ሥርዐት ከባድ ነው። የብሉይ ኪዳኑ ሥርዐትም ለሐዲስ ኪዳኑ ሥርዓት ጥላ ሆኖ አልፏል። 2ኛ ቆሮ 3፥7-11 ፤ ቆላ 2፥17፤ ዕብ 10፥1።

አንባብያን በቀጥታ ወደ ጥያቄው ከመግባታችን በፊት በዚህ ጽሑፍ ዶግማ ላይ ስለዶግማና ቀኖና ማብራሪያ የሰጠነው ይህን ለመሰለው ጥያቄ እንዲጠቅም ነው። አሁን ወደ ሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ስንሄድ ቁም ነገሩ እንደሚከተለው ነው።

የሐዲስ ኪዳን የታቦትና የጽላት አቀራረጽም ሆነ አጠቃቀሙ የተወሰነውና

የሚወሰነው በቀኖና ነው። ቀኖና ደግሞ እንደ ሁኔታው የሚሻሻል ነው። ሲቻል ይጨመርበታል ሳይቻል ደግሞ ይቀነስለታል። እንግዲህ በቤተክርስቲያናችን ቀኖና ካበረከታቸው ነገሮች አንዱ የሐዲስ ኪዳን የታቦትና የጽላት አቀራረጽንና አጠቃቀምን ነው።

ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ለመቅረጽ የግራር እንጨት ባይገኝ በዘፍ 1፥31 ላይ << እግዚአብሔርም የፈጠረውን (ያደረገውን) ሁሉ እጅግ መልካም እንደሆነ አየ>> ስለሚልና እግዚአብሔር የፈጠረውን ስለማይንቅ ከግራር ሌላ ከማይነቅዝ እንጨት መቅረጽ እንችላለን። ቁመቱ ወርዱና ዙሪያውም እንደችሎታችን ይሆናል። በውስጥና በውጭ ስለሚሆነው የወርቅ ክብርም እንደችሎታችን ይወሰናል። ከሌለንም ወርቁ ይቀራል ቀኖና ነውና።

ስለጽላቱም እንደዚሁ ነው ከቻልን ከከበረ ድንጋይ፣ ከዕብነ በረድ መቅረጽ እንችላለን፤ ካልቻልን ጽላቱን ከማይነቅዝ እንጨት መቅረጽ እንችላለን። በሌላ በኩልም ከቻልን እንደ ብሉይ ኪዳኑ በአንድ ታቦት ሁለት ጽላት ማስቀመጥ እንችላለን፤ ካልቻን በአንድ ታቦት አንድ ጽላት ብቻ ይሆናል። በተጨማሪም የጽላቱን ማስቀመጫ ታቦት ባይኖረን ጽላቱን ታቦት ብለን በመጥራት በጽላቱ ብቻ መጠቀም እችላለን ቀኖና ነውና።በተጨማሪም በኤር 31፥31፤ 2ኛ ቆሮ 3፥1-3፤ በዕብ 8፥8-13።

የእኛ አካልና ልቡና የእርሱ ታቦትና ጽላት አልሆነም ወይ? በሐዲስ ኪዳን ለምን ታቦትና ጽላት አስፈለገ? ለምንስ ይህ ሁሉ ተፈጠረ የሚሉ አሉ። የክርስቲያኖች አካልና ልቡና በክርስቶስ ደም ታቦት፤ ጽላት፤ ቤተ መቅደስ መሆኑን እናምናለን። ቢሆንም በሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ያስፈለገበት ምክንያት ስለአምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና

ክብር ሲባል ነው። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ክብሩን የገለጠበት፤ ቃሉን ያሰማበት፣ ሙሴን እንደባልጀራ ያነጋገረበት፣ የክብሩ ዙፋን ሆኖ ጽላቱ በውስጡ ለታቦቱ ማደሪያ በመሆኑ፤ በሐዲስ ኪዳንም የሥጋውና የደሙ የክብር ዙፋን እንዲሆን ሲሆን ስለእኛ በዚህ ዓለም መከራ የተቀበለውን መድኀኔዓለም ክርስቶስን ለማክበር ሲባል ነው።

ጥያቄ 2፡- በዘጸ 31፣18፣32፣15፣134፣1-5።2ኛዜና 5፣10 ያሉትን ጥቅሶች በመጥቀስ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ሁለት ጽላቶችን ብቻ ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እነዚህን እልፍ አእላፋት ጽላቶች ከየት አመጣቻቸው?

አራብታችሁ ቅረጹ የሚል አለ ወይ?

መልስ፡- በዘጸ 32፥19። ስንመለከት እግዚአብሔር ራሱ አዘጋጅቶ ለሙሴ የሰጠውን ሁለቱን ጽላቶች እሥራኤል ጣዖት ሲያመልኩ ስላገኛቸው ሙሴ ተበሳጭቶ ሰብሯቸዋል።ነገር ግን ቸርነቱ ለዘለዓለም የሆነ እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ የመጀመሪያዎቹን አስመስሎ እንዲሰራ ነገረው፤ ሙሴም አስመስሎ ሠራ። ዘጸ 34፥1-5 መሥራት ብቻ ሳይሆን ዐሥሩን የቃል ኪዳን ቃላትም በጽላቶቹ ላይ እንዲጽፍ ሙሉ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ተሰጠው። ሙሴም ተፈቅዶለታልና አሥሩን ቃላት በጽላቶቹ ላይ ጻፈ። ዘጸ 34፥27-28

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጽላትንም ሆነ ታቦትን እያስመሰሉ ለመሥራት ሙሉ ሥልጣንን አግኝተናል። ይህን በተመለከተ አንዳንድ አባቶች እንዲህ ይላሉ፤ <<አዳም እንኳን በደለ አዳም ባይበድል ኖሮ አምላክ ሰው ሆኖ በቀራንዮ ስለእኛ የመሰቀሉን፤ ስለኛ የመሞቱን የፍቅር ምስጢር አናውቀውም

ነበር፡፡>>

እስራኤልም በጥጃ ምስል ጣኦት አምልከው እንኳን በደሉ እሥራኤል ባይበድሉ ሙሴ በእግዚአብሔር የተዘጋጁት ሁለቱ ጽላቶች[1] የሰው ልጅም እግዚአብሔር የሠራቸውን የፊተኞቹን አስመስሎ ለመሥራት ስልጣን ባልኖረውም ቢሠራም ለምን ሠራህ ለሚለው መረጃ ባላቀረበም ነበር>> ይላሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ጽላትን አስመስለን፤ አባዝተን፤ አራብተን ለመሥራት መሠረታችን ሥልጣኑ ለኛ ለልጆቹ የተላለፈልን ከአባታችን ከሙሴ ነው፡፡>> ሙሴ የተሰበሩትን አስመስለህ ሁለት ጽላቶች ቅረጽ ከሚል በቀር ጽላቶችን አብዝታችሁ፤ አራብታችሁ ተጠቀሙ የሚል ቀጥተኛ ቃል አምጡ ለሚለው ግን ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የጽላትም ሆነ የቤተ መቅደስ ሥርዐት፤ የመስዋዕቱ የዕጣኑ አገልግሎት፤ በኢየሩሳሌም ብቻ ስለነበረና፤ የሌላውም አገር ሕዝብ የሚከተለው የጣዖትን ሥርዓት እንጂ የሙሴን ሥርዐት ባለመሆኑ ጽላቱ ተባዝቶ ተራብቶ ለሌላው አገር ሕዝብ አልተሰጠም፡፡ እግዚአብሔርም ከኢየሩሳሌም ውጭ አልፈቀደም የተቀደሰውን ጣዖታውያኑ አሕዛብ ያረክሱታልና ስለዚህ ስግደቱም የቤተመቅደስ ሥርዐቱም በኢየሩሰሳሌም ብቻ ነበር፡፡ /ዮሐ 4፥18-24/

በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ አሕዝቦችም ሠሎሞን ያሠራው ታላቁ ቤተ መቅደስና ሁለቱ ጽላቶች አንሰውናል፤ በርቀት የምንገኝ እኛ የመንገድ ድካም በዝቶብናልና፡፡ ስለዚህ በያለንበት ቤተ መቅደስ ሠርተን ጽላቱን አክብረን መገልገል እንፈልጋለንና ይፈቀድልን ብለው ሙሴም ከሁለቱ ጽላቶች በቀር ሌላ አልተፈቀደም ብሎ መልስ የሰጠበት ቦታ የለም፡፡

ያም ሆነ ይህ በሐዲስ ኪዳንም በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው

በአብ፤ በወልድ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው ፤ሁለተኛ የድኅነት ልደት ተወልደው የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣን ሰጣቸው። ለክርስቲያኖችም ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ እንደሚበዙና በአዲስ ኪዳን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ንጹሕ የሆነውን ቁርባን ከኢየሩሳሌም ውጭ በየቦታው ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንደሚችሉ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

1. << ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ይከበራልና፤ በየስፍራው ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፤ ንጹሕንም ቁርባን ያቀርባሉ፤ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ይላል ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር>> ሚል 1፥11።

2. << ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎ የለምን? እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት ብሎ አስተማራቸው>> ማር 11፥17፤ ኢሳ 56 ፥ 7፤ ኤር 7፥11 ።

ይህ ትንቢት በቀጥታ ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች መሆኑ ግልጥ ነው። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስም ሆነ የዕጣን፤ የቁርባን አገልግሎት እንኳን ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ ላሉ አሕዛብ በኢየሩሳሌም ከሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በቀር ለእስራኤል ጎረቤት አገሮች እንኳ አልተፈቀደምና። ነቢዩ ሚልክያስ ንጹሕ ዕጣን ያለው በማቴ 2፥11። ወንጌል እንደተናገረው ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰብአ ሰገል በቤተልሔም ዋሻ ለክርስቶስ ካቀረቡት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ያለን ክርስቲያኖች በክርስቶስ ስም ለክርስቶስ የምናቀርበው ቅዱስ ዕጣን ነው።

ንጹሕ ቁርባን የሚለውንም በማቴ 26፥26፤ ጌታ ኅብስቱን አንሥቶ ነገ

የሚቆረሰው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ወይኑንም አንሥቶ ነገ ስለብዙዎች ሀጢአት የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው ብሎ ለሐዋርያት የሰጣቸው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። ንጹሕ የተባለው እርሱ በባሕርዩ ንጹሕ ሆኖ የእኛን የኃጢአት እድፍ ስለሚያነጻ ነው።

በብሉይ ኪዳን በኢየሩሳሌም ብቻ መሆን የሚገባቸው ቤተ መቅደሱ፤ ዕጣኑ፣ ቁርባኑ፣ በክርስቶስ ደም በአዲስ ሕይወት፣ በአዲስ ተፈጥሮ፤ በአዲስ ሥርዓት፣ ክርስቲያኖች ለሆንን ለዓለም ሕዝቦች በየሥፍራው (በያለንበት) እንድንጠቀምባቸው ከተፈቀዱልን በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት ሁለቱ ጽላቶች ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ተባዝተው በዓለም ያለን ክርስቲያኖች በያለንበት በየቤተ መቅደሳችን ለሥጋውና ለደሙ የክብር ዙፋንነት ብንገለገልባቸውና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ብናከብርባቸው ምን የሚጎዳ ነገር ተገኘ? የሚያስደነግጠውስ ምኑ ነው? ስህተቱስ የቱ ላይ ነው?

እንዲሁም ዐሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸው ሁለቱ ጽላቶች መባዛት መራባት የለባቸውም ከተባለ በጽላቶቹ ላይ የተጻፉት ዐሠርቱ ትእዛዛት መባዛት የለባቸውም። ከኢየሩሳሌምም መውጣት የለባቸውም ማለት አይደለም? ትእዛዛቱም ተከለከሉ ማለት ነውና።

በጽላቶች ላይ የተጻፉት ትእዛዛት በእግዚአብሔር ፈቃድ በፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ በሚገኙ ክርስቲያኖች እጅ ገብተዋል። ይህም ያስደስታል እንጂ አያሳዝነንም። ይህ ከሆነ ለሥጋውና ለደሙ (ለክርስቶስ) ክብር ሲባል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ጽላቶች ምን በደል አስከተሉ፥ እግዚአብሔር ለቀደሙ አባቶቻችን በታቦቱ

አድሮ የሠራላቸውን ድንቅ ሥራ እያስታወስን እግዚአብሔርን ከማመስገን ውጭ ደግሞም ጌታ ስለ ጸሎት ሲያስተምረን <<አባታችን ሆይ በሚለው ጸሎት ውስጥ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን>> በሉ ብሏል። በዚህ መሠረት በዮሐንስ ራዕይ 11፥19 ላይ ታቦቱን በሰማይ አሳይቶናል። ስለዚህ የሙሴ የቃል ኪዳኑ ታቦት በሰማይ እንዲገኝ፤ በሰማይ እንዲሆን፤ በሰማይ እንዲታይ ፈቃዱ ከሆነ፤ በምድርም እንዲሆን ፈቃድህ ይሁን ብለን ብንጠቀምበት ስህተቱ ምን ይሆን?

ጥያቄ 3፡- የሰሎሞን ቤተ መቅደስ እስኪሠራ ድረስ በእርግጥ ታቦቱ ከቦታ ወደ ቦታ ይዘዋወር ነበር፤ ቤተ መቅደሱ ተሠርቶ ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደሱ ከገባ በኋላ ግን ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ስለመውጣታቸው መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ታዲያ ዛሬ ክርስቶስ ደሙን ካፈሰሰ በኋላ፤ በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን መመሪያ ሳይኖር፤ ከየት አምጥታችሁ ነው ታቦትን በየጊዜው በማውጣት የክርስቲያኖች ህሊና ሁሉ ወደተሰቀለው ክርስቶስ መሆኑ ቀርቶ ወደ ታቦቱ የሆነው?

መልስ፡- በብሉይ ኪዳን እንኳን አይወጣም ነበር ማለት አንችልም ምክንያቱም በችግራቸው ጊዜ ለችግራቸው መፍትሔ ያገኙ ዘንድ ከነበረበት ከድንኳኑም ቢሆን ያወጡት ነበርና ለምሳሌ፦

1. በሙሴ ምትክ የተመረጠ ኢያሱ ሕዝበ እስራኤልን እየመራ ወደ ምድረ ርስት ሲሄድ ድንገት የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶ ባገኘው ጊዜ ወንዙን ከፍሎ አሕዛብን ለማሻገር ከእግዚአብሔር በተነገረው መሠረት ካህናቱ ታቦቱን ከነበረበት ቦታ ተሸክመው ወደ ወንዙ በመሄድ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት እግር ወንዙን ሲረግጥ ወንዙ ተከፍሎ ሕዝቡ ሁሉ በሰላም

መሻገራቸውን እናገኛለን። ኢያሱ 3፥1-17።

2. እስራኤል ምድረ ርስት በደረሱ ጊዜ ምድረ ርስት (ኢያሪካ) በጠላት እጅ በጽኑዕ ግንብ ታጥራ አገኟት። በዚህም ጊዜ ይህን የጠላት የግንብ አጥር ለማፍረስና ርስታቸውን በእጃቸው ለማድረግ እግዚአብሔር የገለጠላቸው ጥበብ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ሕዝቡም እየተከተሉ ሰባት ጊዜ ግንቡን እንዲዞሩት ነው። የታዘዙትን አደረጉ ግንቡም ፈረሰላቸው። ኢያሱ 6፥1-17።

3. እስራኤል ጠላት በበረታባቸው ጊዜ ጠላትን ለማሸነፍ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ይወጡ ነበር። 1 ሳሙ 5፥1-ፍ። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ካህናቱ ታቦቱን ከቦታ ወደ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ካልሆነ በቀር ለሚፈልጉት ዓላማ ታቦቱን ካለት ቦታ ተሸክመው አያወጡትም ነበር ማለት አንችልም። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ካስገባው በኋላ ቢሆንም ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው እንዳያወጡ የሚል ሕግም የለም። እግዚአብሔር የሠራው ሥራ በብሉይ ኪዳን የተፈጸመው አገልግሎት ሁሉ ሙሉ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም። በመጽሐፍ ቅዱስም ያልተጻፈ ብዙ ነገር እንዳለ እናምናለን ከዚህ በመነሳት ነው እኛ በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ተሸክመን የምናወጣው፤

በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ቸርነት (ትእዛዝ) ካህናቱ ታቦታቱን ተሸክመው እንዲወጡ ተደርጎ ካህናቱም ታቦታቱን ተሸክመው በመውጣት በታቦቱ ያደረ ኃይለ እግዚአብሔር ለሕዝበ እስራኤል ያደረገው ድንቅ ሥራ ለማሰብና እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው።ዛሬም ለሥጋና ለደሙ የክብር ዙፋን የሆነውን ቅዱስ ስሙም የተጻፈበትን ቅዱስ ታቦት በምናወጣበት ጊዜ በደሙ የባረከን መድኅነ ዓለም ክርስቶስ አሁንም የሥጋውና የደሙ ዙፋን

በሆነው በታቦቱ ረቂቅ ኃይሎች በማስተላለፍ በረከቱን ያበዛልናል ብለን በማመን ነው።

የተሰቀለው አምላክ መክበሩና መንገሡ ቀርቶ በየጊዜው ታቦት ወጣ እየተባለ ታቦቱ ብቻ ነገሠ ከበረ ሕዝቡም ወደ አምልኮ ባዕድ ኮበለለ ስለሚለው ግን አንድ ሕዝብ የንጉሡን ዙፋን ሲያከብርና ሲፈራ ንጉሡን ማክበሩና መፍራቱ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም።

እኛ የምናምነው ቅዱስ ስሙ የተጻፈበትን የክርስቶስ ሥጋና ደም የክብር ዙፋን የሆነውን ታቦት ማክበራችን በኪሩቤል ዙፋን የሚቀመጥ መድኀነ ዓለም ክርስቶስን ማክበራችን መሆኑን ነው። በታቦቱ ፊት መስገዳችንም በታቦቱ ለተጻፈው ለቅዱስ ስሙ ነው። በታቦት ፊት ለእግዚአብሔር ስም ይሰግዱ የነበሩ ኢያሱና የእስራኤል ሽማግሌዎች በረከት አገኙበት እንጂ አልተጎዱበትምና ነው። ኢያ 7፥6፣ ዘዳ 33፥10።

በሐዲስ ኪዳንም <<ድል ለነሣው ስውር መናን እሰጠዋለሁ፤ የብርሃን መጽሐፍንም እሰጠዋለሁ፤ በዚያ መጽሐፍ ውስጥ ላይ ከተቀበለው በቀር ማንም የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎበታል>> ራእ 217። ለዚህ ስም ደግሞ ጉልበት ሁሉ መንበርከክ እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤

<<ይህም በሰማይና በምድር በቀላያትና ከምድርም በታች ያለ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሰግድ ዘንድ ነው። አንደበትም ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር አብ ክብር ጌታ እንደሆነ ያምን ዘንድ ነው>> ፊልጵ 2፥10-11። በዚህ መሠረት ቅዱስ ስሙ በተጻፈበት ከነጭ ድንጋይ (ከዕምነ በረድ፣ከእንጨት) በተሠራው በጽላቱ ፊት ለቅዱስ ስሙ መስገድ

ታላቅ የመንፈስ ጥበብ እንጂ ሞኝነት አይደለም። ምናልባት ስለታቦት፣ ስለጽላት ባለማወቅ ባጠቃቀሙ በኩል የሚሳሳቱ አባቶቻችን፤ እናቶችን ወንድሞችንና እህቶችን በተገቢው መንገድ ማስተማር ተገቢ ነው።

ከዚህ በላይ ስለ ታቦት ከቤተ መቅደስ መውጣትና አለመውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሆኑ መታወቅ አለበት።

ብዙዎች በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ለመቃወም በኤር 3፥16። የተጻፈውን ጠቅሰው "በዚያ ዘመን ፦የ እስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት እነኋት እያሉም በአፋቸውም አይጠሯትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሿትም።" ተብሏልና ታቦት አያስፈልግም በማለት ያስተምራሉ።

እንደተባለው ታቦት ብሎ መጥራት ካላስፈለገ በኤርምያስ 31፥34፤ ደግሞ "እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፣ እያንዳንዱም ወንድሙን፦ እግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ አያስተምርም" ተብሎ ስለተጻፈ እንግዲህ ሰው ሁሉ በየዘመኑ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ማስተማር አያስፈልግም ማለት ነዋ! ደግሞም ጌታችን በማቴ 28፥19 "እንግዲህ ሂዱና በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ" ብሎ መናገሩ ስህተት መሆኑ ነዋ! በአጠቃላይ እንዲህ ነው ብሎ ከመናገር አስቀድሞ በመጽሐፍ የተጻፈው ነገር ለምንና እንዴት ባለ ሁኔታና ጊዜ መጻፉን ማጥናትና መልእክቱን (ምስጢሩን) መመርመር ይገባል እንላለን።

በመጨረሻ ግን በኢትዮጵያ ኦርቶኮክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማርያም፣ የቅዱሳን፣የሰማዕታት፣ የመላዕክት ወዘተ.... ታቦት እየተባለ የተሰየመበት ምክንያቱና የዚህ ስያሜ ከየት ነው የመጣው ምንድን ነው የሚሉ ጥያቄዎች

ሊኖሩ እንደሚችሉ እርግጥ ነው።

እንዲህ ተብሎ መሠየሙ በትንቢተ ኢሳይያስ 56፥46 በተገለጸው መሠረት የእግዚአብሔርን ሰንበቱን ለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘውንም ለሚመርጡ ቃል ኪዳኑንም ለሚይዙ ጃንደረቦች (ስለእግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸውን ጃንደረባ ያደረጉ ቅዱሳን) ማቴ 19፥12 በእግዚአብሔር ቤትና በቅጥሩ የዘለዓለም መታሰቢያ እንደሚደረግላቸው የተገለጠ በመሆኑ ይህን አብነት በማድረግ ጌታ ሥጋው፣ ደሙ የሚከብርበት ሆኖ ለቅዱሳኑም መታሰቢያ ለማድረግ ነው። /መዝ 111፥7/ እንዲሁም የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነውና ምሳ 10፥7። በዚህ ምክንያት እንጂ በታቦታቱ የሚከብረው መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ መሆኑ ግልጽ ሊሆን ያስፈልጋል።

እናም መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በኤስራኤላውያን ባህልና የአኗኗራቸው ዘይቤ ተከትሎ ነው።ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የኤስራኤላውያን ባህልና የአኗኗ ማወቅ ያስፈልጋል። ይህን ለማወቅ የግድ ኤስራኤል መሄድ ኣይጠበቅባቹም፤የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ዶግማና ቀኖና ይህንኑ ስለሚያሳዩ።

ለምሳሌ የማርያም ጠባቂ ይሆን ዘንድ ኣረጋዊው ዮሴፍ መንፈስ ቅዱስ መርጦ በመልኣኩ ለምን <<የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ>>ኣለው?

እግዚአብሔር አስተዋይ ልቡና ይስጠን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አሜን።

ምንጭ፦ መጽሐፍ ቅዱስ

ትምህርት ሃይማኖት (የሃይማኖት ትምህርት)